# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 162 የካቲት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!













ፎቶ፡ ሔዲስ አብርሃ

# ግጭቶችን ለማስቆምና ሠላምን ለማረጋገጥ
## የሚሠሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ኅብረት በአህጉሪቱ የሚከሰቱ ግጭቶችን ለማስቆምና ሠላምን ለማረጋገጥ የሚሠሩ ሥራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አዲሱ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበር ገለጹ።

አዲሱ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበር የሞሪታኒያው ፕሬዚዳንት መሐመድ አወልድ ጋዝዋሀኒ በ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ መዝጊያ መርሐ ግብር ላይ እንደተናገሩት፤ መሪዎቹ በቆይታቸው የአጀንዳ 2063 የመጀመሪያ አስር ዓመት አፈጻጸምን በመገምገም የቀጣዩ አስር ዓመት እቅድ ላይ ተወያይተዋል።

ባለፉት ጊዜያት በተለይም በሠላም ማስፈን፤ በሰብዓዊ


ግጭቶችን ለማስቆምና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# የኢትዮጵያ
## ጎረቤት ሀገራት ወደብን በተመለከተ ከታንዛኒያ ልምድ መውሰድ አለባቸው

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ወደብን በተመለከተ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገራት ከታንዛኒያ ልምድ መውሰድ እንዳለባቸው በታንዛኒያ የኢትዮጵያ


የኢትዮጵያ ጎረቤት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





**«ኢትዮጵያ ለኅብረቱ ጉባዔ የመጡ እንግዶችን ሁሉ ያለ ልዩነት ተቀብላ በማስተናገድ በስኬት አጠናቃለች»**

- *ሠላማዊት ካሣ*
  *የመንግስት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታ*


ገጽ 4


# «ከኅብረቱ ጉባኤ በተጓዳኝ የኢትዮጵያን ልክ ያሳዩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ተከናውነዋል»

- ቢልለኔ ሥዩም
  የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በተጓዳኝ የኢትዮጵያን ልክ ያሳዩ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች መከናወናቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ ቢልለኔ ሥዩም ገለጹ። ከኅብረቱ ስብሰባ ጎን ለጎን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከ15 ሀገራት በላይ መሪዎችን አግኝተው የሁለትዮሽ ውይይቶችን አካሂደዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ያደረጓቸውን የሁለትዮሽ ውይይቶችና 37ኛውን የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ አስመልክቶ ቢልለኔ ስዩም በሰጡት ማብራሪያ እንዳመለከቱት፤ በኅብረቱ ስብሰባ ወቅት ኢትዮጵያ ልኳን ማሳየት ያስቻሉ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ተግባራትን አከናውናለች።


«ከኅብረቱ ጉባኤ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ቢልለኔ ሥዩም







# በአፍሪካ የጥይት ድምፅ እንዳይሰማ ለማድረግ ኅብረቱና መንግሥታቱ ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ

## - ኅብረቱ ስድስት ሀገራትን ከአባልነት አግዷል

**ሄለን ወንድምነው**


አምባሳደር ባንኮሌ አዴኦዬ

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ የጥይት ድምፅ እንዳይሰማ በማድረግ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ኅብረቱና መንግሥታቱ ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ ሲሉ የአፍሪካ ኅብረት የፖለቲካ ጉዳዮች፣ ሠላምና ደኅንነት ኮሚሽነር አምባሳደር ባንኮሌ አዴኦዬ ገለጹ። ከአፍሪካ ኅብረት አባልነት ስድስት ሀገራት መታገዳቸውም ተመላክቷል።

የአፍሪካ ኅብረት የፖለቲካ ጉዳዮች፣ ሠላምና ደኅንነት ኮሚሽነር አምባሳደር ባንኮሌ አዴኦዬ ከ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በተጓዳኝ የአህጉሪቱን የፀጥታ ጉዳዮች አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፣ በአህጉሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተቀሰቀሱትን ግጭቶች በመፍታት ዘላቂ ሰላም ለማስፈን በትኩረት እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

በአፍሪካ ሽብርተኝነት፣ ጽንፈኝነት፣ ግጭት፣ ኢ-ሕገመንግሥታዊ የመንግሥት ለውጥና ሌሎችም የፀጥታ ሥጋቶች የአህጉሪቷ ፈተና ሆነው መቀጠላቸውን ገልጸው፣ ይህ አካሄድ ለአፍሪካ ዘላቂ ልማት መሳካት እንቅፋት መሆኑን ገልጸዋል።

በአህጉሪቷ ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት እንዲፈጠር የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥና ሕገ መንግሥታዊ አሠራርን መከተል ይገባል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ ከሕገ መንግሥታዊ አሠራር ውጭ ሥልጣን ለመያዝ የሚደረግ እንቅስቃሴ በምንም አይነት መልኩ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን አስታውቀዋል።

በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግርና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ኅብረቱ ድጋፍ የሚያደረግ ሲሆን፣ ከሕግ ውጭ የሆኑ አሠራሮችን እንደማይታገስ አፅንዖት ሰጥተው ተናግረዋል።

ኅብረቱ በአፍሪካ ዘላቂ ሰላምን በማስፈን የጥይት ድምፅ እንዳይሰማ ለማድረግ ሁሉንም አካላት ያሳተፈ የሠላም ግንባታ ሥራዎችን እንደሚሠራ ገልጸው፣ የአፍሪካ መሪዎችም ለዘላቂ ሰላም መስፈን የሚሠሩት ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

የሀገራት መሪዎች በአህጉሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የተቀሰቀሱትን የፀጥታ መደፍረሶች በመፍታት መልካም አስተዳደር፣ ዴሞክራሲ እና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት በጋራ እንዲሚሠሩ በስብሰባቸው ትኩረት ሰጥተው መወያየታቸውን ገልጸዋል።

የአፍሪካ ኅብረት ኢ-ሕገመንግሥታዊ የመንግሥት ለውጥ የሚያደርጉ ሀገራትን እንደማይታገስ ገልጸው፣ ስድስት ሀገራት ተግባሩን በመፈጸማቸው እና የኅብረቱን የዲሞክራሲ መርሆዎች በመጣሳቸው ከአፍሪካ ኅብረት ተሳትፏቸው መታገዳቸውን አስታውቀዋል።

ከአባልነት የታገዱ ሀገራት ጋቦን፣ ኒጀር፣ ጊኒ፣ ሱዳን፣ ቡርኪናፋሶ እና ማሊ መሆናቸውን ገልጸው፣ ሀገራቱ እርምጃ የተወሰደባቸው ከድርጊታቸው ተምረው ዴሞክራሲን እንዲለማመዱ ለማድረግ መሆኑን አስረድተዋል።

ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ ዘላቂ ልማት መሳካት መሠረት በመሆናቸው ኅብረቱ ኢ-ሕገመንግሥታዊ የመንግሥት ለውጥ ባደረጉ ሀገራት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን፣ የሕግ የበላይነት፣ ሰብዓዊ መብት እና መሠረታዊ የነፃነት መብቶችን እንዲከበሩ ድጋፍ ሊደረግ እንደሚገባም አብራርተዋል።

በአፍሪካ ሽብርተኝነት፣ ጽንፈኝነት፣ ኢ-ሕገ-መንግሥታዊ የመንግሥት ለውጥ፣ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፣ የአመፅ ድርጊቶች አሁንም በአፍሪካ ፈተና ሆነው ቀጥለዋል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ በእነዚህ ችግሮች ምክንያት በአህጉሪቱ ያለው የፀጥታ ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ብለዋል።

ግጭት አላስፈላጊ በመሆኑ ተፋላሚ ኃይሎች ጠመንጃቸውን አስቀምጠው ወደ ጠረጴዛ በመምጣት ልዩነታቸውን በውይይት እንዲፈቱ ጠይቀዋል።


ጫልቱ ታምሩ

# 40 ሺህ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወደ 10 ሺህ ሊጠቃለሉ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በለውጥ ሂደቱ (በሪፎርሙ) ተመሳሳይ የሆኑ 40ሺ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማዋሓድ ወደ 10ሺ ማኅበርነት ሊጠቃለሉ መሆኑን የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ጫልቱ ታምሩ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ እንደ ሀገር የኅብረት ሥራ ማኅበራቶችን የፋይናንስ አቅም ለማጎልበትና የሰው ኃይል አጠቃቀም ለማዘመን የሪፎርም ሥራ ተጀምሯል።

በሀገሪቱ ከ28 ሚሊዮን በላይ አባላትን የያዙ አንድ መቶ አስር ሺህ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መኖራቸውን ጠቁመው፣ እነዚህ ማኅበራት 49 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ካፒታል ማስመዝገባቸውን አመላክተዋል።

በኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የፋይናንስ እጥረት ብሎም የሰው ኃይል የአቅም ውስንነት በመኖሩ ከተቋቋሙበት ዓላማ አኳያ የሚጠበቀውን ውጤት ሳያመጡ መቆየታቸውን አስረድተዋል።

የማኅበራቱ የፋይናንስ እንዲሁም የሰው ኃይል አቅማቸው ያልጠነከረ ከመሆኑ በተጨማሪ በርካታ ማኅበራት ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩ እንዲሁም ፈቃዳቸው አንድ ዘርፍ ላይ ሆኖ ነገር ግን ሁለገብ የንግድ አገልግሎቶች የሚሰጡ ናቸው ብለዋል።

ስለሆነም የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የጠነከሩና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ለማስቻል ሪፎርም ማድረግ ማስፈለጉንና ውሕደት የሚፈጸም መሆኑን አመላክተዋል።

በዚህም ኮሚሽኑ ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ነገር ግን በአቅማቸው ያልጎለበቱ 40 ሺህ ማኅበራትን እንዲዋሐዱ በማድረግ ወደ 10 ሺህ ለማምጣትና በበየው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ዕቅድ መያዙን አስታውቀዋል።

የተሻሉ የሚባሉ ማኅበራት ውሕደት ሳይፈጥሩ ባሉበት አቅማቸው እንዲያጠናክሩና ተፅዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

በለውጥ ሂደቱ አተገባበር ላይ የክልል ኅብረት ሥራ ማኅበራትና አመራሮች እንዲሁም፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ተወካዮች የተሳተፉባቸው ውይይቶች መደረጋቸውን አንስተዋል።

በተለይም በድሬዳዋ ከተማና በኦሮሚያ ክልል ማኅበራቱን ሪፎርም የማድረጉ ሥራ የተጀመረ ሲሆን፣ በሌሎች ክልሎች ላይም ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ኃላፊዋ ጨምረው ገልጸዋል።



# ኢትዮጵያ በአፍሪካ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ እንዲሆን የሚደረገውን ጥረት ትደግፋለች

**ታደሠ ብናልፈው**

ሱሉልታ፡- ኢትዮጵያ በፓን አፍሪካ ወጣቶች ማኅበርና ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ወጣቶች በመላ አፍሪካ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ እየሠሩት ያለውን ሥራ ተፈፃሚ ለማድረግ በትኩረት እንደምትሠራ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ባለፉት ሦስት ቀናት በአፍሪካ የልህቀት አካዳሚ የአፍሪካ መሪ ወጣቶች ጉባኤ የተካሄደ ሲሆን በጉባኤውም ለአፍሪካ 21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን፣ ጥራት ያለው፣ ሁሉን አካታች ትምህርትን በአፍሪካ ተደራሽ በማድረግ ዙሪያ የቃልኪዳን ስምምነት ተደርጓል።

በጉባዔውም የማጠናቀቂያ ንግግር ያደረጉት የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ(ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ወጣቶች በመላ አፍሪካ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ የደረሱበትን የቃልኪዳን ስምምነት ተፈፃሚ ለማድረግ ትኩረት ሰጥታ ትሠራለች ብለዋል።

የአፍሪካ ወጣቶች የትምህርት ጥራት ተደራሽነት ለፖሊሲ አውጪዎችና ለመንግሥታት ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም ያሉት ሚኒስትሯ፣ የአፍሪካ ወጣቶች የትምህርት ሥርዓቱ እንዲሻሻል ያደረጉት ሥራ እኛ ያላየነውን እንድናይ አድርጎናል ብለዋል።

ከፓን አፍሪካ ወጣቶች ማኅበርና ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ወጣቶች በአፍሪካ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ተወያይተው የቃልኪዳን ስምምነት አድርገዋል፣ ይህም ተፈፃሚ እንዲሆን ኢትዮጵያ በትኩረት ትሠራለች ሲሉ ገልጸዋል።

ትምህርት የሁሉ ነገር ቁልፍ መፍቻ ነው፣ የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊና የሰው ሀብት ልማት ችግርን ለመፍታት፣ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካዊ መፍትሔ ለመስጠት ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊና ተገቢም ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

ወጣቶች አፍሪካ የትምህርት ጥራት እንዲሻሻል እያደረጉት ያለው ሥራ መንግሥታት ያላዩትን ክፍተት የሚሞላ፣ ለችግሮቻችን አፍሪካዊ መፍትሔ የሚሰጥ ነውም ብለዋል።

ትምህርት የሰውን ልጅ እውቀት፣ ልምድ ከማስፋትና ከማሳደግ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት የሚያመጣ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ጥራት ያለው ትምህርት በመላ አፍሪካ ተደራሽ እንዲሆንና የቀጣይ ሀገር ተረካቢዎችን ራዕይ ብሩህ ለማድረግ ኢትዮጵያ የምትችለውን ሁሉ ታደርጋለች ሲሉ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ የሱፍ መሐመድ በበኩላቸው፣ ለአፍሪካ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ የወጣቶች ሚና ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ጥራት ያለው ትምህርትን ለአፍሪካ ተደራሽ ማድረግ ሁለተናዊ እድገት ለማስመዝገብና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ይጠቅማል ብለዋል።

ሀገር በቀል እውቀትን በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በማካተት ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ማድረግ ተገቢ ነው፣ ይህንንም ለማድረግ ከአፍሪካውያን ወጣቶች ጋር በጋራ እንሠራለን ሲሉ ገልጸዋል።

በአፍሪካ ጥራት ያለው፣ ክፍለ ዘመኑን የሚመጥን፣ ሁሉን አቀፍና አካታች የሆነ የትምህርት ሥርዓት ተደራሽ ለማድረግ ወጣቶች በጋራ እንሠራለን ሲሉ የፓን አፍሪካ ወጣቶች ማኅበር ዋና ፀሐፊ አቶ አሕመድ ቢኒንግ ገልጸዋል።

በመላ አፍሪካ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ እንዲሆን የፓን አፍሪካ ወጣቶች ማኅበር በትኩረት እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

# የኢትዮ-ኬንያ የሚኒስትሮች ስብሰባ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ይበልጥ ያሳድጋል

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- 36ኛው የኢትዮ-ኬንያ የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባ የሁለቱን ሀገራት ወዳጅነትና የጋራ ተጠቃሚነት የሚያሳድግ መሆኑን በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ባጫ ደበሌ አስታወቁ።

36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ትናንት መካሄድ ጀምሯል። ስብሰባው ሦስት ቀን የሚቆይ ሲሆን በተለያዩ ዘርፎች የሁለትዮሽ ስምምነቶችን በመፈራረም በነገው ዕለት ይጠናቀቃል።

በውይይቱ ወቅት ለጋዜጠኞች መግለጫ የሰጡት በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ባጫ ደበሌ እንደገለጹት፤ 36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ከብዙ ዓመት በኋላ የተደረገ ነው።

ይህ ስብሰባ በኮቪድ አስራ ዘጠኝና በተለያዩ ምክንያቶች ላለፉት ሰባት ዓመታት ሳይካሄድ መቆየቱን የጠቀሱት አምባሳደር ባጫ፣ ከሰባት ዓመት በኋላ ከሁለቱ ሀገራት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን እያካሄዱ ነው ብለዋል። በነገው እለት የሁለቱ ሀገራት ሚኒስትሮች ስብሰባ ይካሄዳል።

ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር ከ35 በላይ ልዩ የሆኑ የሁለትዮሽ ስምምነቶችን አድርጋለች ያሉት አምባሳደሩ፤ በ36ኛው የጋራ ስብሰባ መጨረሻ ላይ የሚኖሩ ስምምነቶች የቆዩትን ልዩ ስምምነቶች የሚያጠናክሩ ይሆናል ብለዋል።

አዲሱ የኬንያ የቪዛ አሠራር በስብሰባው በዋናነት የሚነሳ ጉዳይ መሆኑን ገልጸው፤ አዲሱ ቪዛ ከኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ለመሄድ አስቸጋሪ ነገር ስለፈጠረ ችግሩን ለመፍታት የኬንያ መንግሥት እየሠራ ነው ብለዋል። በአጀንዳነትም የተያዘ በመሆኑ ችግሩ ይፈታል ተብሎ እንደሚገመት ገልጸዋል።

በስብሰባው በተለያዩ ዘርፎች ብዙ የሁለትዮሽ ስምምነቶች ይኖራሉ ያሉት አምባሳደር ባጫ፤ የስብሰባው ዋና ዓላማ በውጭ ጉዳይና በመከላከያ፤ በንግድና ኢኮኖሚ እንዲሁም በማኅበራዊ እድገት ጉዳዮች ዙሪያ ያተኮረ መሆኑን ጠቅሰዋል። በሦስቱ ዘርፎች ሰፊ ውይይቶችን በማካሄድ የጋራ አዳዲስ ስምምነቶች እንደሚኖሩም ይጠበቃል ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ባጫ ገለጻ፤ እየተደረጉ ያሉ የጋራ ስብሰባዎችና የሁለትዮሽ ስምምነቶች በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ሲውሉ የነበሩ ናቸው። በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል ረጅም እድሜ ያስቆጠረና ታሪካዊ ግንኙነት አለ። ይህን ታሪካዊ ግንኙነት በየጊዜው በተደማሪ ውጤቶች አጅቦ ለማስቀጠል 36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ወሳኝ ነው። ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራ ለማስመዝገብም የሚያስችል ነው።

በኬንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር ሌምሸሯ ሞኢ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በ36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት በሚያጠናክሩ በውጭ ጉዳይና በመከላከያ፤ በንግድና ኢኮኖሚ ጉዳዮችና በማኅበራዊ እድገት ዙሪያ ውይይቶች ይደረጋሉ። ስምምነቶችም ይኖራሉ።

ከሰባት ዓመት ቆይታ በኋላ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ መካሄዱ ለኬንያ ልዩ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በተለይ ዓለም አቀፍና ቀጣናዊ ተለዋዋጭ የፖለቲካ ጉዳዮች ባሉበት ወቅት ስብሰባው መደረጉ ልዩ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል።

ኢትጵያና ኬንያ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር በሁለትዮሽ፣ በቀጣናዊ፣ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቋሚ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። የሁለቱን ሀገር ታሪካዊ ግንኙነት ለማስቀጠል የሁለትዮሽ ስምምነቶችን መከለስ፣ ሁለቱ ሀገራት በተለያዩ ዘርፎች የተፈራረሟቸውን የሁለትዮሽ ስምምነቶች ውጤታቸውን መገምገምና የሁለቱን ሀገራት ሕዝቦች የወደፊት ተጠቃሚነት ማብራራት እንደሚገባ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ጠቁመዋል።



ፎቶ፡ ሐዲስ አብርሃ

# ዩኒቨርሲቲው የስንዴ ምርታማነትና የአርሶአደሮችን ሕይወት ለማሻሻል እየሠራ ነው

**ማርቆስ በላይ**

ባሌ ሮቤ፡- ዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም የስንዴ ምርታማነትና የአርሶአደሮችን ሕይወት ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት አሕመድ ከሊል(ዶ/ር) ገለጹ።

በስንዴ ምርታማነት ላይ ያተኮረ ሀገር አቀፍ ሲምፖዚየም በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ እየተካሄደ ነው።

የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሕመድ ከሊል በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለፁት፤ ዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም የስንዴ ምርታማነትና የአርሶአደሮችን ሕይወት ለማሳደግ እየሠራ ነው።

እንደ ዶክተር አሕመድ ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲው በግብርና ቱሪዝም ብዝኃ ሕይወትና በጤና ዘርፎች በትኩረት እየሠራ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲው በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አርሶአደሮችን በመደገፍ ላይ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ መንግሥት የስንዴን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ባስቀመጠው "ኢኒሼቲቭ" መሠረት ድጋፍ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የባሌ አካባቢ በግብርናው ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆን ዩኒቨርስቲው ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው በስንዴ ምርታማነትን በማሳደግ አርሶአደሩን ተጠቃሚ በማድረግ ውጤታማ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል።

የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንት በዛብህ ወንድሙ(ዶ/ር) በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማርና ምርምርን ጨምሮ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል።

ከመማር ማስተማር ተግባሩ በተጨማሪ የማኅበረሰቡ ችግር የሚቀርፉ ምርምሮችን እያደረገ ይገኛል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በሕክምናው ዘርፍ በጎባ ሪፈራል ሆስፒታል የሕክምና አገልግሎትን ለማኅበረሰቡ እየሰጠ ይገኛል ብለዋል።

የስንዴ ምርትና ምርታማነትን መጨመር ዩኒቨርስቲው እየሠራባቸው ከሚገኙ ሥራዎች አንዱ መሆኑን ጠቅሰው ባለፉት አምስት ዓመታት የአካባቢውን አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ዩኒቨርስቲው የአርሶአደሩን ምርት ለማሳደግ የተለያዩ ድጋፎችን እንደሚያደርግ በመግለጽ ከኬምቴክስና ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን ፀረ አረም መድኃኒቶችን፣ የአፈር ማዳበሪያዎችንና የተለያዩ ግብዓቶችን ማቅረባቸውን አስረድተዋል።

በሲምፖዚየሙ የስንዴን ምርታማነት የተመለከቱ የተለያዩ 12 ጥናትና ምርምሮች እንደሚቀርቡ ገልጸው በተለይም የስንዴን ምርታማነትና የአርሶአደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ግብዓት እንደሚሆን አመላክተዋል።

በመርሐግብሩ የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት የምርምር ማዕከላት ዳይሬክተሮች የሀገር አቀፍ የስንዴ ኢኒሼቲቭ አስተባባሪዎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ በግብርና ኢንዱስትሪው የተሰማሩ ግለሰቦችና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# ለቀይ ባሕር አካባቢ ደህንነት መረጋገጥ የኢትዮጵያን ሚና ወሳኝነት አለው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ቀይ ባሕርን ጨምሮ አጠቃላይ ለቀጣናው ደህንነት መረጋገጥ የኢትዮጵያ ሚና ወሳኝነት አለው ሲሉ የፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪው አቶ ሺመልስ ኃይሉ ተናገሩ።



አቶ ሺመልስ ኃይሉ

አቶ ሺመልስ ኃይሉ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ለቀይ ባሕር ቀጣና ሠላምና ደህንነት መረጋገጥ የኢትዮጵያን ሚና ማየት አስፈላጊ ነው።

ኢትዮጵያ በታሪክ፤ ለአካባቢው ካላት ቅርበትና ለቀጣናው ሠላምና መረጋጋት ከሠራቻቸው ሥራዎች አንጻር ያላትን ሚና አሳንሶ መመልከት አይገባም ሲሉ አስረድተዋል።

በቀይ ባሕር አካባቢ የሚፈጠሩ የተለያዩ ውንብድናዎችንና የባሕር ላይ ወንጀሎችን እንዲሁም የተለያዩ ችግሮችን ለመከላከል የተቋቋመ ምክር ቤት መኖሩን የጠቀሱት አቶ ሺመልስ፤ በምክር ቤቱ ምሥረታ በአካባቢው ሰፊ ሕዝብ ያላትና ተፅዕኖ መፍጠር የምትችለውን ኢትዮጵያን አለማካተቱ ትልቁ ችግሩ ነው ብለዋል።

በምክር ቤቱ አባል የሆኑ ሀገራት አንዳንዶቹ ከቀይ ባሕር ራቅ ብለው የሚገኙና አንዳንዶቹ ደግሞ ሠላም ያልሰፈነባቸው ሀገራት መሆናቸውን አንስተው፤ በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ሀገራት አቅማቸውን አጠንክረው ለአካባቢው ደህንነት በጋራ እንዲሠሩ የሚመለከታቸውን ሀገራትም ማካተት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ ሺመልስ እንደተናገሩት፤ የቀይ ባሕር ቀጣና የዓለም 10 በመቶ የሚሆነው ንግድ የሚመላለስበት በመሆኑ ከኢኮኖሚ ሆነ ከሠላም አንጻር ወሳኝ አካባቢ ነው።

በአካባቢው ላይ ባለፉት ዓመታት እየተጠናከረ የመጣው ሽብርተኝነት፣ የአልሸባብ መስፋፋት፣ የየመን አለመረጋጋት እና የተለያዩ ጥቃቶች መጠናከር ለቀጣናው ስጋት የደቀነ ነው ብለዋል።

ችግሩን ለማቃለል ኢትዮጵያን የምክር ቤቱ አባልና የባሕር በር ተጠቃሚ እንድትሆን በማድረግ የራሷን ጥቅም አስጠብቃ ለአካባቢው ሠላም ደህንነት እንድትቆም ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ያላት ርቀት 60 ኪሎ ሜትር የማይሞላ እንደመሆኑ በአካባቢው የሚፈጠር ማንኛውም ችግር ሀገሪቱን ይመለከታል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ሺመልስ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ጠንካራ የወታደር ኃይል ያላት እንደመሆኗና በቀጣናው የሱማሊያን ጨምሮ የሌሎች ሀገራትን ሠላምና መረጋጋት ለማረጋገጥ ስትሠራ የቆየች ሀገር እንደመሆኗ በቀይ ባሕር ፖለቲካ ውስጥ ወሳኝ ሚና ሊኖራት ይገባል።

በታሪክ ረገድም ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር በርካታ ወደቦችን ስታስተዳድር የነበረች ሀገር እንደመሆኗ፤ አካባቢውን ከመጠበቅ አንጻር አቅሙና ልምዱ አላት ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የምክር ቤቱ አባል ለመሆንና ለቀጣናው መረጋጋት የራሷን ድርሻ እንድትወጣ የሌሎች ሀገራትም ድጋፍ ያስፈልጋል፤ አንዱን ባገለለ መልኩ የሚከናወን ልማትና ሰላም ዘላቂ አይሆንም ብለዋል።

በተጨማሪም እርስ በርስ የሚፎካከሩ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ሩሲያ፣ ሳዑዲ ዓረቢያና የተባበሩቱ ዓረብ ኤምሬቶች በአካባቢው የጦር ልምምድ እያደረጉ መሆኑን አንስተዋል።

ሀገራት ችግር ውስጥ ቢገቡ ቀድሞ ጦርነት የሚነሳው በቀጣናው ነው፤ ይህም በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ሀገራትን ስለሚጎዳ ኢትዮጵያም በቀጣናው ዋነኛ ተዋናይ ሆና የምትቀጥልበትን አማራጭ ማስፋት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ዜና

# «ኢትዮጵያ ለኅብረቱ ጉባዔ የመጡ እንግዶችን ሁሉ ያለ ልዩነት ተቀብላ በማስተናገድ በስኬት አጠናቃለች»

- ሠላማዊት ካሣ
  የመንግስት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ለመሳተፍ የመጡ እንግዶችን ሁሉ ያለ ልዩነት በመቀበል ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ደረጃን በጠበቀ መልኩ አስተናግዳ በስኬት ማጠናቀቋን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ። 37ኛውን የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ ትናንት የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍ መጠናቀቁ ተመላክቷል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሠላማዊት ካሣ 37ኛውን የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ መጠናቀቅ አስመልክተው ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፤ ኢትዮጵያ 37ኛውን የመሪዎች ጉባዔና 44ኛውን የሥራ አስፈጻሚዎች መደበኛ ስብሰባ ለመሳተፍ የመጡ የአፍሪካ መሪዎችን፣ ሚኒስትሮችን እና የተለያዩ የዓለም ሀገራት መሪዎችን ተቀብላ በማስተናገድ በስኬት አጠናቃለች።

የኅብረቱ አባል ሀገራት መሪዎች የደህንነት ስጋት እንዳይገጥማቸው ኢትዮጵያ ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዳ መሥራቷን አስገንዝበው፤ ለጉባኤው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ መሪዎችን ክብራቸውን በሚመጥን መንገድ ወደ ሀገራቸው መመለሷን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ለጉባዔው ለስድስት ወራት ያህል ዝግጅት እንዳደረገች ገልጸው፤ በዚህም የኅብረቱን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና የአባል ሀገራት መሪዎች የክብር አቀባባል ተደርጎላቸዋል ብለዋል።

ለጉባዔው ስኬታማነት በርካታ ተቋማት በቅንጅት የተሳካ ሥራን አከናውነዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የፀጥታ አካላት፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ሚዲያዎችን እና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን አመስግነዋል።

አባል ሀገራቱ ጉባኤውን በሚገባ ተከታትለው ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ መንግሥት እና ሕዝቡ ውጤታማ ሥራ ስለመሥራታቸውም ተናግረዋል።

በጉባዔው አፍሪካ ትክክለኛውን ለውጥ ለማምጣት በትምህርት በተለይም በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የተደገፈ የትምህርት ዘርፍ ላይ ሊሠሩ እንዲገባ በስፋት መነሳቱን አመላክተው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የትምህርት ጥራትንና ተደራሽነትን ለማስፋፋት እያከናወነች ያለውን ተግባር በጉባኤው መክፈቻ ስለመናገራቸው አስታውሰዋል።

37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ ደማቅና የተሳካ ነበር ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ኢትዮጵያም ጉባዔውን ከማዘጋጀትና ከማሳካት ባለፈ ብሔራዊ ጥቅሞቿን በማስከበርና በውጭ ግንኙነት ያላትን ከፍታ ያፀናችበት እንደነበርም ገልጸዋል።

ከሀገራት ጋር የተደረጉ የሁለትዮሽ ውይይቶችና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ ምክክሮችም ውጤታማ መሆናቸውን እና ከመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን ኢትዮጵያ ያዘጋጀችው ጉባኤ በዓድዋ ድል መታሰቢያ መካሄዱንም ጨምረው ተናግረዋል።

የጉባዔው መሳካት እንዳለ ሆኖ በሶማሊያ መንግሥት በኩል ጉባዔውን ለማወክ እና ዓለም አቀፍ ትኩረት ለማግኘት የተነሱ ያልተገቡ ክሶች እንዲሁም የጦር መሣሪያ ይዞ ወደ ጉባኤው ለመግባት መሞከር፣ በአባል ሀገራት መሪዎች ተቀባይነትን ያላገኙ ሆነው ማለፋቸውን እንዲሁም በኅብረቱ የፀጥታና የደህንነት አካላት ወዲያውኑ መፈታት እንደተቻለ አስታውቀዋል።

የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐሙድ ኢትዮጵያ ሲገቡ ለሁሉም ሀገራት በተደረገው ልክ ደማቅ አቀባበል እንደተደረገላቸው ገልጸዋል።

የተለመደው አሠራር መሪዎች ሲመጡ አቀባበል ብቻ ሳይሆን ጥበቃ የሚደረገውም በአስተናጋጅ ሀገር ሲሆን፤ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐመድ የጥበቃ ድጋፉን አልቀበልም ማለታቸውን አስረድተዋል።

ከየካቲት 9 እስከ የካቲት 10 ቀን 2016 ዓ.ም ሲካሄድ የቆየው 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት መደበኛ የመሪዎች ጉባኤ ትናንት የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ተጠናቋል።

ጉባኤው "ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን አፍሪካዊ ማስተማር፤ የማይበገሩ የትምህርት ሥርዓቶች በመገንባት በአፍሪካ ሁሉን አቀፍ፣ የሕይወት ዘመን፣ ጥራትና አግባብነት ያለው የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት" በሚል መሪ ሀሳብ መካሄዱንም አስታውሰዋል።



አምባሳደር ሽብሩ ማሞ

# የኢትዮጵያ ጎረቤት ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አምባሳደር ሽብሩ ማሞ አስታወቁ።

በታንዛኒያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሽብሩ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ሁለገብ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ ለውጥ ውስጥ ትገኛለች።

እያደገ የመጣውን 120 ሚሊዮን ሕዝብ መሸከም የሚችል ኢኮኖሚ ለመፍጠር ቀጣይነት ያላቸው ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል ያሉት አምባሳደር ሽብሩ፤ ለዚህ ደግሞ የወደብ ጉዳይ ቅንጦት ሳይሆን ግዴታ ነው። በሰጥቶ መቀበል መርሕ ወደቦችን ማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን አይገባም ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ገለጻ፤ ታንዛኒያ ከጎረቤቶቿ አልፋ አፍሪካን ለመጥቀም የምታደርገውን ጥረት የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገራት እንደተሞክሮ ሊወስዱት ይገባል።

ተባብሮ መልማት ግጭትን በማስቀረት የልማት ትብብርን ያፋጥናል ያሉት አምባሳደር ሽብሩ፤ በኢትዮጵያና በሶማሊላንድ መካከል የተደረሰው የባሕር በር ስምምነት ለቀጣናው አንድነት ሲባል ሊደገፍ ይገባል ብለዋል።

አምባሳደር ሽብሩ እንዳሉት፤ ስምምነቱን የሚቃወሙ ሀገራት ከታንዛኒያ መማር አለባቸው። ታንዛኒያ ሰባት ወደቦች ያሏት። ለምሥራቅ አፍሪካ ማኅበረሰብ ሀገሮች የወጭና ገቢ ምርት ከማመላለስና አገልግሎት ከመስጠት ውጭ ለዛምቢያ 20 ሄክታር ደረቅ ወደብ ሰጥታለች። ይህም ለጋራ እድገት ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ነው። በመሆኑም ሌሎች ሀገራት ከታንዛኒያ መማር አለባቸው ብለዋል።

በርካታ ሀገሮች ከሩቅ መጥተው በሶማሊላንድ የባሕር በር በሊዝ ሲከራዩ ምንም አልተባለም ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ስትከራይ ለምን ጫጫታው በዛ የሚለው በራሱ መፈተሽ አለበት ብለዋል።

የኢትዮጵያ ወታደሮችና ዜጎች ሕይወታቸውን ለሶማሊያ በመስጠት በሠላም እንዲኖሩ አድርገዋል፤ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ትልቅ ውለታ ውላለች። ይህን ከግምት በማስገባትና ያላትን የሕዝብ ብዛት በመገንዘብ ታንዛኒያ ለጎረቤቶቿ እንደምታደርገው ሁሉ የኢትዮጵያም ጎረቤት ሀገራት የባሕር በር ሊሰጧት ይገባ ነበር ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ማብራሪያ፤ የዛምቢያ ሸቀጥ በታንዛኒያ ወደብ ላይ እስከ 45 ቀናት ያለ ቀረጥ እንዲቆይ ፈቃድ ሰጥታለች። ይህ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲታይ ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር ሰጥቶ በመቀበል መርሕ ወደብ ለማግኘት የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መፈራረሟ በቀጣናው የጋራ ተጠቃሚነትን ያመጣል። ሶማሊላንድ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ተመጣጣኝ አክሲዮን ይኖራታል። በሁለቱ ሀገራት በኩል የተደረሰው ስምምነት የተለመደና ሌሎች ሀገራት እየተጠቀሙበት ያለ ልምድ ነው ብለዋል።

የታንዛኒያን ተሞክሮ ተባብሮ ለማደግ መልካም አመለካከት ያላቸው ሌሎች ሀገራትም ይህን በማስፋት አፍሪካውያን በጋራ ሠርተው ማደግን ባሕል ማድረግ አለባቸው ብለዋል አምባሳደሩ።

ኢትዮጵያ ከድህነት እንዳትወጣ የሚፈልጉ አካላትና ሀገራት ህዳሴ ግድቡን ሲቃወሙ ነበር ያሉት አምባሳደር ሽብሩ፤ ኢትዮጵያ ወደብ እንዳታገኝ የሚደረገው ማስፈራራት ተቀባይነት አይኖረውም። እንዲሁም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ከመገዳደር ተለይቶ አይታይም ብለዋል።

# ግጭቶችን ለማስቆምና ሠላምን ለማረጋገጥ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሙብት ጥበቃ፤ በመልካም አስተዳደርና አስተማማኝ ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ረገድ ጥሩ የሚባሉ ለውጦች ተመዝግበዋል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ እነዚህን በማስቀጠል ሠላም ለማስፈንና ግጭቶችን ለማስቀረት እንዲሁም የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣናን ውጤታማነት ለማረጋገጥ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

በዓመቱ መሪ ሀሳብ መሠረትም በአፍሪካ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመንን የሚመጥን ጥራት ያለው የትምህርት ተደራሽነት እንዲረጋገጥ መሥራት ይጠበቃል ብለዋል።

በተጨማሪም አፍሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ቅቡልነት ለማጠናከርና በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት ለማድረግ፤ እንዲሁም ለራሳችን ችግሮችና ለሚገጥሙን ተግዳሮቶች የራሳችንን መፍትሔ በድርጅታችን በኩል እንድናቀርብና እንድንተገብር መሥራት የሚጠበቅ ይሆናል ብለዋል።

ስብሰባው "ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን አፍሪካዊ ማስተማር፤ የማይበገሩ የትምህርት ሥርዓቶች በመገንባት በአፍሪካ ሁሉን አቀፍ፣ የሕይወት ዘመን፣ ጥራትና አግባብነት ያለው የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት" በሚል መሪ ሀሳብ ሲካሄድ መቆየቱ ይታወሳል።

# «ከኅብረቱ ጉባኤ በተጓዳኝ የኢትዮጵያን ልክ ያሳዩ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ዓድዋ ሙዚየምን በማስጎብኘት፣ ጉባኤውን በስኬት ማከናወንና ከፍ ባለ መንገድ የእራት ግብዣ የአህጉሪቷን መሪዎች ተቀብሎ ማስተናገድ የተቻለበት መንገድ የኢትዮጵያን ልክ ያሳየና የተሳካ ዲፕሎማሲያዊ መስተጋብር የፈጠረ ነው።

"በከተማዋ ላይ ያለውን ለውጥ ያስተዋሉትን ለማጋራት የቻሉበት አጋጣሚዎችም ነበሩ፤ ምስክርነቶቹም በርካታ ለውጦች እንዳሉና ይህም አስደስቷቸዋል። ሁልጊዜ አዲስ አበባ የኅብረቱ መቀመጫና የአፍሪካ ዋና ከተማ ተብላ ስለምትታወቅ ይህንን ጥሩ ተሞክሮዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች አንስተዋል" ሲሉም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጉባኤው ከመሳተፍ ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት መሪዎች ጋር ስኬታማ የሁለትዮሽ ውይይቶች አድርገዋል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) ከአፍሪካ ኅብረት የወቅቱ ሊቀመንበርና የሞሪታንያ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ከሆኑት መሐመድ አወልድ ጋዝዋሀኒ ጋር በአህጉሪቷ ጉዳዮች ላይና በጋራ መሥራት ስለሚቻልባቸው ጉዳዮች መምከራቸውን ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

የሞሪታኒያውም ፕሬዚዳንት በበኩላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ሀገሪቷን ለመለወጥ ያላቸውን ራዕይና የሄዱበትን ርቀት ማድነቃቸውነ ቢልለኔ አመላክተዋል።

በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የታንዛኒያውን ፕሬዚዳንት ሳሚያ ሱሉሁ ሃሳን ጋር ገንቢ ውይይት ማድረጋቸውንና የቀድሞው የታንዛኒያ መሪ ጁሊየስ ኔሬሬ ሐውልት አፍሪካ ኅብረት ጊቢ ውስጥ በቆመበት ሰዓት ላይም ተገናኝተው የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

የውይይታቸው ትኩረት በምስራቅ አፍሪካ ጉዳዮች ላይና ሁለቱም ሀገራት በሚያተኩሩባቸው የኃይል አቅርቦት ዘርፍ በትብብር መሥራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ መሪ ፊሊክስ ትሺሴኬዲ ጋር መምከራቸውን ቢልለኔ ተናግረው፤ በአህጉሪቷ የሚስተዋሉ የሠላምና ደህንነት አለመረጋጋቶችን መቅረፍ የሚቻልባቸው አማራጮች ላይ ውይይት ማካሄዳቸውን አስረድተዋል።

በተጨማሪም ሁለቱም ሀገራት ለአህጉሪቷ ያላቸውን ተስፋና ራዕይ እውን የሚሆንበትን መንገድ ከሌላ ሀገራት መሪዎች ጋር ምን መደረግ እንዳለበት ሀሳብ መለዋወጣቸውን ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዩኤንዲፒ አፍሪካ የቢሮ ዳይሬክተር አሁና ኢዚአኮንዋ ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን ኃላፊዋ አመላክተው፤ የወጣቶችን ሥራ አጥነት ለመፍታት በሚከናወኑ ርምጃዎች ላይ መምከራቸውን ጠቁመዋል፤

ዘመኑ የቴክኖሎጂ እንደመሆኑ ወጣቶች ያላቸውን አቅም ተጠቅመው ሀገራቸውንም ሊለውጡ በሚችሉባቸው ጉዳዮችና አህጉሪቷ የፈጠራ መስክ የምትሆንበት አግባብ በምን በኩል መፍጠር እንደሚቻል ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

ቢልለኔ እንዳስታወቁት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በውይይቱ ወቅት ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ እየሄደችበት ያለውን ርቀት ማቅረብ ችለዋል።

በአጠቃላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሁለት ቀናት ቆይታ በርካታ ውይይቶችን የተደረጉበትና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን በማሳደግ ላይ ያተኮረ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ ከ37ኛው የኅብረቱ ጉባኤ ጋር ከ11 የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ጋር የሁለትዮሽ ወይይቶችና አጠር አጠር ባሉ አጋጣሚዎች ደግሞ ከአራት በላይ የተለያዩ ሀገራት መሪዎችን አግኝተው መወያየታቸውን አመላክተዋል።

በሌላ በኩል ከኅብረቱ ጉባኤ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የብራዚሉን ፕሬዚዳንት ሊዊዝ ኢናሲዮ ሉላ ዳ ሲልቫን አግኝተው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸው ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን ታላቅነት ያረጋገጠ ስኬታማ ጉባኤ!

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ትልቅ ስትባል፤ የትልቅነቷ መሠረት የሆነው እና በትልቅነቷ እንድትገለጥ ያደረገው ሕዝቧ ነው። ትልቅ ሕዝብ ደግሞ ትልቅ ሀገር የሚሠራ እንደመሆኑ በትልቅነት ውስጥ ታላቅ ሆኖ መዝለቁ እሙን ነው። ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ይሄው የጎብር ገጻቸው የሆነው ትልቅነትና ታላቅነት ታዲያ፤ በሁሉም ቦታና በሁሉም ሁነትና ሁኔታ እየተገለጠ የዘለቀ ነው።

ትናንት በአልበገር ባይነቱ የነፃነትን ቀንዲል ለመላው አፍሪካውያን እና ጭቁን ሕዝቦች ያቀበለው ይሄ ኢትዮጵያዊነት ታዲያ፤ ዛሬም ከትናንት አባቶቹ በወረሰው የፓን አፍሪካኒዝም ልዕልናው አፍሪካውያንን በአንድ እያሰባሰበ ወደ ምሉዕ ሉዓላዊነታቸው እንዲሸጋገሩ እየተጋ ይገኛል።

ኢትዮጵያን የነፃነት ምልክትም፣ የዓለም ዲፕሎማሲ ማዕከልም እንድትሆን ያደረገው ይሄ ታላቅነት ታዲያ፤ አዲስ አበባም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ከተማነቷን የሚመጥን ኃላፊነቷን በብቃት እንድትወጣ እያደረጋት ይገኛል። በዚህም ሀገራዊ፣ ቀጣናዊ፣ አኅጉራዊ እና ዓለምአቀፋዊ የመሪዎችም፣ የተቋማትም ጉባኤዎችን በስኬት የምታስተናግድ ከተማ ሆናለች።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይነት ጎልቶ የሚጠቀስ ተግባር ነው። ይሄ ሕዝባዊ እሴት ደግሞ እንግዶች በክብር ተቀብሎ ወደሚያስተናግዳቸው ሕዝብ ደጋግመው እንዲያማትሩም፣ እንዲመላለሱም የሚያደርግ ሲሆን፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገነባ የመጣው የፀጥታና ደኅንነት ኃይሉ አቅም ደግሞ እንግዶች ስጋት እንዳያድርባቸው እያደረገ ይገኛል።

በዚህም ኢትዮጵያ በርካታ ዓለምአቀፍ ሁነቶችን ለማስተናገድ ተመራጭ ሀገር እየሆነች መጥታለች። በዛው ልክ የሕዝቦቿን ልዕልና፤ የዲፕሎማሲ መንገዷን ስኬታማነትም እየገለጠች ትገኛለች። የየትኛውም ዓለም መሪና ተቋም፣ አልያም ተወካይ ያለ ስጋት የሚጎበኛት፤ ያለ ችግር የሚስተናገድባት፤ ያለ መሳቀቅ ጉዳዩን ፈጽሞ የሚመለስባት ትልቅ ሀገርነቷንም እያስመሰከረች ነው።

የሰሞኑ 37ኛው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤም የዚህ አንድ ማሳያ ሲሆን፤ በተለይ ብዙዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ሠላም የለም በሚል ሂደቱን ለማደናቀፍ ሲውተረተሩ የነበረበትን ሁነት ቀዝቃዛ ውሃ የቸለሰበት ነበር። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የደረሰችበትን ደረጃ፤ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ ለአፍሪካውያን ወንድም ሕዝቦችና መሪዎቻቸው ያላቸውን ከፍ ያለ ቦታ በአደባባይ የገለጠ ሆኗል።

ምክንያቱም፣ ጉባኤው የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ፣ ኢትዮጵያ እንደ ኅብረቱ መቀመጫ ሀገርነቷ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጋለች። በተለይ ከሠላምና ፀጥታ፣ ከሆቴልና ሌሎችም የሎጀስቲክስ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ተገቢው ዝግጅት ተደርጓል። በጥቅሉም መሪዎቹ ለጉባኤው መሳካት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ውስጥ ሙሉ ደህንነትና ምቾታቸው ተጠብቆ እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል።

መሪዎቹ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ጀምሮ ተገቢው አቀባበል የተደረገላቸው ሲሆን፤ በሆቴል ቆይታቸው ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያደርጓቸው ዝግጅቶችም ነበሩ። በከተማዋ በሚኖራቸው ቆይታም የደህንነት ሥጋት እንዳይሰማቸው ያደረገው የፀጥታ ኃይሎች ዝግጅት በተግባር የተገለጠባቸው ሁነቶች ደግሞ ለጉባኤው በስኬት መጠናቀቅ የነበራቸው አበርክቶ ከፍ ያለ ድርሻ ነበረው።

በተለይ ቀደም ብሎ ሲራገብ ከነበረው አሉባልታ አኳያ የፀጥታና ደህንነት ኃይሉ ሲያከናውን የነበረው ከፍ ያለ ተግባር፤ ኢትዮጵያ ከትናንቱ በላቀ መልኩ ዛሬ በዘርፉ አቅም መገንባቷን፤ ነገም የትኛውንም አህጉራዊም ሆነ ዓለምአቀፋዊ ሁነት ያለምንም የፀጥታ ሥጋት ማካሄድ እንደምትችል አቅሟን የገለጠችበት ሆኗል።

የፀጥታና ደህንነት ኃይሉ ደጀን የነበረው እንግዳ ተቀባዩ ሕዝብም፣ ለኅብረቱ ጉባኤ መሳካት የነበረው አበርክቶ ተኪ የሌለው ነው። በጥቅሉ የኅብረቱ ጉባኤ በስኬት ለመጠናቀቁ፣ የፀጥታ ኃይሉ ትጋትና ቅንጅት፤ እንዲሁም የሕዝቡ ተባባሪነትና እንግዳ ተቀባይነት ወሳኝ ነበር።

ለዚህ አኩሪ ተግባርም ሁሉም አካል ሊመሰገንም፤ ተገቢውን እውቅና ሊቸርም የሚገባው ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ቤታቸው፣ ኢትዮጵያውያንንም ሕዝባችን ብለው በጉባኤው በመሳተፍ ለጉባኤው ስኬታማነት የድርሻቸውን ለተወጡ አፍሪካውያን ወንድም መሪዎችም ክብርም፣ ምስጋናም ይገባቸዋል። ምክንያቱም የዚህ ድምር ውጤት ጉባኤው በስኬት እንዲጠናቀቅ ብቻ ሳይሆን፤ የኢትዮጵያን ትልቅነት፣ የኢትዮጵያውያንንም ታላቅነት አረጋግጧልና!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሰማዕታት የሚታወሱበት ዕለት!

**ሠላማዊት ውቤ**

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መቼም ቢሆን ከማይረሱት አሳዛኝ ቀናት መካከል የካቲት 12 ከግንባር ቀደሞቹ ተርታ የሚቀመጥ ነው። በ1929 ዓ.ም በዚህ ቀን በፋሽሽት ኢጣሊያ ወታደሮች በኢትዮጵያውያን ላይ የተፈፀመው ጭፍጨፋም እለቱን አሳዛኝ የሚያደርገው ዋነኛ ምክንያት ነው።

ከታሪክ ማኅደር እንደምንረዳው የጭፍጨፋው መነሻ የኔፕልስ ልዕልት በመወለዷ በዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድሮው ቤተመንግሥት የኢጣሊያው አለቃ ግራዚያኒ ባዘጋጀው ፌሽታ ድግስ ላይ ቦንብ መወርወሩ ነው።

በወቅቱ ግራዚያኒ የልዕልቷን ልደት ለኢትዮጵያውያን ድሆች ምፅዋት በመስጠት የማክበር ፍላጎት ነበረው። ምፅዋቱ ደግሞ ሁለት ማርትሬዛ ብር መሆኑንም ገልጿል። በዕለቱ ቀትር አካባቢ ይሄንኑ ምፅዋት ብለው ሦስት ሺህ የሚሆኑ ድሆች ወደ ቤተ መንግሥቱ አቅንተዋል። በዓለ ልደቱንም ኢትዮጵያውያኑን መኳንንቶች ጨምሮ የኢጣሊያኑም ሹማምንቶች ተገኝተዋል ።

የታሪክ መዛግብት እንደሚሉት ፌሽታው አህዱ ሳይባል አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በዓሉ ከሚደረግበት ቦታ ቀደም ብለው ደረሱ ... ሁለቱም በኪሶቻቸው ቦንብ ይዘዋል፣ ማርሻል ግራዚያኒ ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ሲያደርግ የፋሽሽት ኢጣሊያ መኩዋንንት ካሉበት ቦታ የያዙትን ቦንብ ወረወሩ። አጋፋሪው ግራዚያኒ ጀርባውን በቦንቡ ክፉኛ በመመታቱ ቆስሎ ወደቀ።

ከዚህ በኋላ በነበሩት የተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥም ሌሎች ቦምቦች ተከታትለው ተጣሉ። በወቅቱ እነዚህን ጨምሮ በጠቅላላው በግቢ ውስጥ ሰባት ቦምቦች እንደፈነዱ በወቅቱ የነበሩ የዓይን ምስክሮችን ዋቢ ያደረጉ የታሪክ ጸሐፍት ይናገራሉ።

ግራዚያኒ ቦንቦች ሲወረወሩ እሱ ጠረጴዛው ሥር በመደበቁ በጣም ተጎድቶ በፍጥነት ወደ ሆስፒታል ሲወሰድ። ሌሎቹ ደግሞ ራሳቸውን ከቦምብ ለማዳን በያሉበት መሬት ይዘው በመተኛት ከአደጋው መትረፍ ችለዋል። የቦንብ ጥቃቱን ተከትሎ ከኢጣሊያ ሹማምንት እና የሲቪል ወታደሮች በግቢው በተሰበሰበው ሕዝብ ላይ ለተከታታይ ሦስት ሰዓታት ባገኙት ኢትዮጵያዊ ላይ ተኩስ በመክፈት በሀገሪቱ ታሪክ ያልታየ አሰቃቂ እልቂት ፈጽመዋል።

በእልቂቱም በክብር ተጋብዘው በፌሽታው ከታደሙትና የግድያው ሰለባ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ሹማምቶችና መኳንንቶች፤ በተጨማሪም አዛውንቶች፤ ሁለቱን ማርትሬዛ ብር እመፀወታለሁ ብለው የመጡ ዓይነ ስውራን፤ እጅ እግር የሌላቸው፤ የተለያየ አካል ክፍሎቻቸው የጎደሉ ድሆች፤ እናቶች ከእነ ልጆቻቸው በግፍ ተገድለዋል ።

> **በእልቂቱም በክብር ተጋብዘው በፌሽታው ከታደሙትና የግድያው ሰለባ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ሹማምቶችና መኳንንቶች፤ በተጨማሪም አዛውንቶች፤ ሁለቱን ማርትሬዛ ብር እመፀወታለሁ ብለው የመጡ ዓይነ ስውራን፤ እጅ እግር የሌላቸው፤ የተለያየ አካል ክፍሎቻቸው የጎደሉ ድሆች፤ እናቶች ከእነ ልጆቻቸው በግፍ ተገድለዋል**

ጨካኞቹና ባለ ጥቁር ሸሚዞቹ፤ የኢጣሊያ ሹፌሮች፤ የቅኝ ግዛት ወታደሮች፤ ሦስት ሰዓታት ያህል በስፍራው የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ጨፍጭፈው አላበቁም። በበቀል ስሜት በአዲስ አበባ ከተማ እየዞሩ ኗሪውን ጨፍጭፈዋል። በንጹሐንና ሠላማዊ ዜጎች ላይ ያለምንም ከልካይ ባገኙት ላይ ተኩስ ይከፍቱ፣ በያዙት ቤንዚንም ከ10 እና ከ20 በላይ ቤቶችን በመደዳ ያቃጥሉ፣ በየቤቱ እየተዟዟሩም ብር እና ወርቅ ይዘረፉ ነበር።

የብርና ወርቁ ዘረፋ ሳይበቃቸው የከተማዋን ነዋሪ ከቤቱ ጭምር ቤንዚን በማርከፍከፍ በእሳት ያጋዩ ሲሆን ጭሱ አዲስ አበባን እንዳጨለማት፣ ነፍስ ይዞት እሳቱን እየሸሸ የሚወጣውን ነዋሪ እየጠበቁ በመትረየስ እንደፈጁት ይነገራል። እየሸሸ በየቤተክርስቲያኑና በየቦታው የተደበቀውን ነዋሪም እያሰሱ ይገድሉት ነበር።

በጨካኙ ግራዚያኒና መሰሎቹ እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው በእሳት እየተቃጠሉ እንዲሁም በጥይት እየተደበደቡ ይገደሉ ተብሎ የተፈረደባቸው በመሸሸ ላይ የነበሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አያሌ ቁጥር ነበራቸው። «አዛኝ ቅቤ አንጓች» እንደሚባለው ከጨካኞቹ ጣሊያኖች ውስጥ ሲሸሹና በፍተሻ ተደብቀው የተገኙና ነዋሪዎች በእሳት ተቃጥለው ከመሞት ይልቅ በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ አዛኝ የሚያስመስላቸው ትዕዛዝ ያስተላለፉበትም ነበር።

ግራዚያኒ ለሕክምና በገባበት ሆስፒታል መስኮት አንገቱን ብቅ አድርጎ በጭፍጨፋው ደሙ እንደጎርፍ የሚወርደውንና ሬሳው በየቦታው የተረፈረፈውን የከተማዋን ነዋሪ እያየ በመሳቅ ይዝናና ነበር። ከሚያማልሉ አውቶሞቢላቸው በመውረድ በዚህ ደምና ሬሳ ላይ ቆመው እንደሱ የሚዝናኑትንና የሚስቁትን ጣሊያናውያን ያበረታታም እንደነበርም የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ።

ለተከታታይ ሦስት ቀናት ጨካኙ ግራዚያኒና ጭፍሮቹ በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ ባደረሱት በአሰቃቂ ግፍ የተሞላ ጭፍጨፋ 30ሺ ነዋሪዎች ተገድለዋል። ቀሪዎቹ እየታፈሱ በረሃ ውስጥ ወደሚገኝ እስር ቤት ተግዘዋል።

የካቲት 12 ለሀገር ክብርና ነፃነት ሲሉ ከወራሪ ኃይል ጋር የተፋለሙና የተዋደቁ ጀግኖች የሚታወሱበት እለት ነው። የኢትዮጵያውን የአንድነትና አይበገሬነታቸው አንዱ ማሳያ ነው። እለቱ የሚታሰበው በፋሽስቱ ኢጣሊያ በግፍ የተጨፈጨፉትን ብቻ ሳይሆን፤ ሀገር ምን ያህል ዋጋ ተከፍሎባት አሁን ላይ መድረሷን ለማስታወስ ጭምር ነው ።

**ዘለዓለማዊ ክብር በግፍ ለተጨፈጨፉት ሰማዕታት!!!**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የታላቁ ዓድዋ ድል ምስጢር

**(የመጨረሻ ክፍል)**

በመጀመሪያ ክፍል መጣጥፍ የጦርነቱን አነሳስና የጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን የውጊያ ስትራቴጂ አጋርቻለሁ። በዛሬው መጣጥፍ ደግሞ የቀሩ የውጊያ ስልቶችንና የዓድዋን ግዙፍ አንድምታ አወሳለሁ።

3ኛ የውጊያውን እምብርት የማፍረስ የመጨረሻው ታክቲክና ቅንጅት፡- የኢትዮጵያ ሠራዊት የአልቤርቶኒንና የዳቦርሜዳን የክፍተት ስህተት ተገንዝቦ በየስፍራው ጠላትን የመምታት አቅሙን በተግባር ባዋለበት በዚያች ሰዓት በወታደራዊ ጠበብቶች እይታ የኢትዮጵያ ሠራዊት ለሀገራቸው የዓድዋን ድል ማስመዝገባቸው የታወቀ ጉዳይ ሆኖ ነበር። የበርሃው መብረቅ የበጋው ብራቅ የዶጋሊው አራስ ነበር ራስ አሉላ አባ ነጋ በፍጥነት ይህ አጋጣሚ ሳይቆይ እንዲተገበር ወሳኝ የጦር መሪ ሆነዋል። ይህንን ጉዳይ ሲተገብሩ ራስ አሉላ ለንጉሠ ነገሥቱ ያስተላለፉት መልዕክት በመድፍ፣በመትረየስ፣በጠመንጃ ስለወጠርናቸው በአስቸኳይ የኦሮሞ ፈረሰኞች ከራስ ሚካኤል ጦር ውስጥ በብዛትና በፍጥነት አካባቢውን እንዲያጥለቀልቁትና ከምሥራቅ አቅጣጫ መንገድ ዘግተው በጨበጣ የኢጣሊያኑን ኃይል እንዲለቅሙ ብለው ስለተመካከሩ ውጊያዎቹ ድልን በድል ላይ ጨመሩ።ጦርነቱ አልቋል ውጊያዎች ግን ቀኑን ሙሉ ተካሄዱ።

ከጠዋቱ 3 ሰዓት ተኩል ጀምሮ በሌላ አቅጣጫ ወደ ወጊያው የገባው የአርሞንዲ ሠራዊት በተራው ተመታ። በሁሉም አቅጣጫ በጥልቅት የኢጣሊያን ወራሪ ኃይል በቀለበት ውስጥ በማስገባት ሙት፣ቁስለኛ፣ምርኮኛ ማድረጉን አረጋገጠ። ይህንን የመሰለ የውጊያ አቅም ተጠቅመው በጄኔራል ዳቦር ሜዳ ፣በጄኔራል አርሞንዲ፣በጄኔራል ኤሌና ተዋናይነት በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተው የሮማ ቄሳር ጦርነት ፣የቅኝ ግዛት ዓላማው አልቤርቶኒና ዓድዋ የሕልም እንጀራ ሆነ። የዓድዋ የድል የሕልም እንጀራ እንዲሆን አደረገው!!

ስለላ እና የዓድዋ ድል፡- በራስ አሉላ አባ ነጋ እና በራስ መንገሻ በኩል በቂ አቅም የነበራቸው እና ግሩም ሥራ የሠሩ የመረጃ ሰዎች ነበሩ። በሚስጥር የተዘረጋው የመረጃ መረብ ዕርዳታና ድጋፍ የኢትዮጵያ ዘማች ሠራዊት በኢጣሊያ የጠላት ሠራዊት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና እንዲያሳድር ረድቷል። በሻይ አውዓሎምና በራስ አሉላ እና በራስ መንገሻ ሥር የነበሩት ሌሎች ሰዎች የመሬትና የባህል እውቀት፣የቋንቋ ችሎታና ከኢጣሊያኑም ጋር በነበራቸው የውስጥ ለውስጥ የመረጃ ሥራ ብዙ ዘዴ በማካበት የሰጡት መረጃ ኢጣሊያኑን ሠራዊት በሚጎዳና የውጊያውን አጀማመር ኢትዮጵያውያኑን ዘማች ሠራዊት በሚጠቅም መልኩ በማድረጋቸው አስተዋፅኦአቸው እጅግ የጎላ ነበር።

የራስ ስብሀትና የደጃዝማች ሐጎስ ከኢጣሊያን ወገን ከድተው ወደ ኢትዮጵያ ሠራዊት መቀላቀል ብዙ መረጃዎችንም ይዞ ስለመጣ ሁኔታዎች ሁሉ ለኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንዳይመቻች አድርጎታል።የዘማቹ ሠራዊት ቆራጥነትና ብርታትም ሌላው ጀብዷዊ የታሪክ አንጓ ነው። ሠራዊቱ አልጋውን ለማቆም እንጂ ለመሸሽ አይፈልግም።አንዱ ወደ ፊት አንዱ ወደ ኋላ አይልም(መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፡የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ) ላይ እንደ ዘገቡት። ኢትዮጵያዊ ጀግንነት ተስተውሏል።ኢትዮጵያዊ ፅናት በእጅጉ ተንፀባርቋል። በመላው ዓለምም አብርቷል።

የዓድዋ ድል ለእኛ ትውልድ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው? ኢትዮጵያ አሁን ላይ በርካታ የውጭም የውስጥም ድጋቶች ተደቅነውባታል። የመፍትሔ መንገዶችን እያማተረች ፣የቢሆን መላምቶችን

> **ዓባይ ለኢትዮጵያ ወንዝ ብቻ አይደለም ባህል፣ሃይማኖት ፣ እምነት፣ፍልስፍና፣ ቅኔ እና አፈር ነው። ካይሮዎች ይህን በበላይነት ያለ ማንም ከልካይነት መዝረፍ ይፈልጋሉ**

እያፍታታች ባለበት ወቅት በእርግጥ የዓድዋ ድል እና የዚያ ዘመን የነፃነት አርበኞች ምን መልዕክት ያስተላልፉልናል ብሎ መጠየቅ ብልህነት ይመስለኛል። እስኪ የእነርሱን አስደማሚ ጀብድ ጅማሮ እና ፍፃሜ ሰዓታት ላይ የነበሩ እልሆችን ከታሪክ ድርሳናት እንግለጥ።

ከዘመቻው ጉዞ ሂደት ጀምሮ እስከ ጦርነቱ መጨረሻ ድረስ ዝግመት፣ክፍተት፣ ቅፅበት መመካከርና መከባበር በስፋት የነበሩ ክስተቶች ናቸው። በጦርነቱ ወቅት አልጋ በአልጋ የሚሆን ነገር ስለማይኖር በእነዚያ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ታልፎ የዓድዋ ድል እውን ሆኗል። የእንጢጮን ተራራ በ27 ቀን በፀሐይ በሌሊት በሙብራት የተገነባውን፣የተደለደለውን ትቶ እንደ ተመረዘ ጉሬዛ ከሜዳ ላይ ተዘርግፎ እንደ እህል ተወቃ። ስፍራውን ቢያበጁ፣መሣሪያ ቢያደራጁ ጉልበትና ብልሀት የእግዚያብሔር መሆኑ በዚህ ተገለጠ (ፀሐፊ ገብረ ሥላሴ ገፅ 257) አስፍረውታል።

ከጦርነት ድል በኋላ የተመላሹ ቁጥር ሳስቷል። ዘምተውና በውጊያው ከነበሩት ጀግኖች ውስጥ እነ ፊታውራሪ ገበየሁ ጎራው፣ደጃዝማች ጫጫ፣ደጃች ባሻህ አቦዬ፣ፊታውራሪ ተክሌ፣ቀኝ አዝማች ታፈሰና ሌሎች ያልተጠቀሱት ቁጥራቸው የበዛ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የዓድዋ ጦርነት ወኪል ዋልታና ማገር በነበሩበት ብዙኃን ውስጥ ወደ ቄያቸው አልተመለሱም። የድሉን ጎዳና አፋጥነው በዚያው በእነዚያ የጥቁር ሕዝቦች መመኪያ የዓድዋ ተራሮች ህያው ሆነዋል። ይህ ትውልድ ከቅድመ አያቶቹ እና አባቶቹ የሰነቁለትን አስተምህሮት በተራው ለወቅታዊው ችግሮች መፍትሄ ሊጠቀምበት ይገባል።

ትናንት ለዓድዋ ጦርነት መነሻ የሆነው የውሃ ጦርነት ዛሬም ለሌላ ጦርነት እያዘጋጀን ይሆን? ግብፅ እንደ እንግሊዝ ሱዳን እንደ ኢጣሊያ ጊዜው 19ኛው ክፍለ ዘመን አይደለም። 21ኛው ክፍለ ዘመን ነው። ቴክኖሎጂ መር 4ኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የተቀጣጠለበት። ምሥራቅ አፍሪካ በተለይም የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ ፖለቲካ ደግሞ ዛሬም እንደ ትናንቱ ተፈላጊነቱ እጅግ ያሻቀበበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ይህ ቀጣና ከግሪክ እስከ ሮማኖች፣ከኦቶማኖች እስከ ፈርኦኖች፣የቅኝ ግዛት እስከ ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ፣ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች እስከ ቀዝቃዛው ጦርነት ገፈት ቀማሽ ሆኗል። አሁን ደግሞ በአዲሱ የእጅ አዙር ጦርነት መዳፍ ውስጥ ለመግባት በወደብ እና ጦር ሰፈር ግንባታ ከኃያላን እስከ ህዳጣን ከነዳጅ ከበርቴዎች እስከ ኒዩክሌር አረር ባለቤቶች ከፍተኛ ርኩቻ እየተካሄደበት ነው።

በመጀመሪያ ክፍል መጣጥፍ የዓድዋ ጦርነት ስረ መሰረት መነሻ እንግሊዝ በኢጣሊያን በኩል የዓባይ ወንዝን የመቆጣጠር ህልም ነበር። የዓድዋ ጦርነት ዋና ግብ ጣሊያን የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት መመዝበር በተለይም የዓባይ ወንዝን ነበር። ለፋብሪካዎቿ ጥሬ እቃ ፍለጋ እና በቀጣናው ያላትን ተስፋፊነት እና ተሰሚነት ማጎልበቻ ነበር።ያኔ ጀግኖች አርበኞቻችን የኢትዮጵያ የነፃነት ንስሮች ከሁሉም የሀገራችን ክፍል ነጋሪት ጎስመው ወደ ዓድዋ ተመሙ። የቄራስ ኃይላት በጥሬ እቃ ምዝበራ የታወሩ ግን ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያን በሚገባ ያላወቁት ሰላቶዎች በዓድዋ ተራሮች የኢትዮጵያን ጀግኖች ጎራዴ ፉጨት መቋቋም ተሳናቸው። የዓድዋ ተራሮችም ለእነዚያ ቄሳር ኃይላት ተላላኪዎች የጎን ውጋት ሆኑባቸው። ምዕራባዊያን ለረዥም ዘመን የዘሩት የሀሰት ተረክ በዓድዋ ባዶ ሆነ። ነጮች በጥቁሮች አይሸነፉም የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ለፈፋ በዓድዋ ባዶ ሆነ።

አፍሪካዊያን እና መላው የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ብሎም በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር የነበሩት ሌሎች ሀገራት ፓን ኢትዮጵያኒዝምን እየሰበኩ የቅኝ ግዛት ቀንበርን እስከ ወዲያኛው ጠረማመሱት። የጣሊያን የጥሬ እቃ እና የተፈጥሮ ሀብት ምዝበራ የባህል ክለሳ በዓድዋ ተደመሰሰ። የዓባይ ፖለቲካ ዛሬም ድረስ በቅኝ ግዛት ዘመን ውሎች ተሸብቦ በአዲሱ የቅኝ ግዛት እሳቤ የተሸበቡት ፈርዖኖች። ዛሬም በ1929 እና 1959 ስምምነት የመሟገቻ እና የአሳሳች ዲፕሎማሲያቸው መጋመጃ አድርገው እየባዘኑ ነው። የግብፆች ግብ እንደ ጣሊያኖች የቅኝ ግዛት መንፈስ የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት መመዝበር ነው።

ዓባይ ለኢትዮጵያ ወንዝ ብቻ አይደለም ባህል፣ሃይማኖት ፣ እምነት፣ፍልስፍና፣ ቅኔ እና አፈር ነው። ካይሮዎች ይህን በበላይነት ያለ ማንም ከልካይነት መዝረፍ ይፈልጋሉ። እርግጥ ሲዘርፉም ከርመዋል። ሱዳን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሲጀመር ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አቋሟ ከኢትዮጵያ ጎን ነበር።ነገረ ኦማር ሀሰን አልበሽር በዳቦ አብዮት ከስልጣናቸው ሲፈነገሉ ውሃው ዲፕሎማሲም አብሮ የተቀለበሰ ይመስላል። ግብፅ እንደ ኢንግሊዝ ሱዳን እንደ ኢጣሊያ እየሆኑ መጥተዋል። በዚያኛው ክፍለ ዘመን እንግሊዝ የዓባይን ወንዝ ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር ሱዳን እና ግብፅ የሚገኙ የጥጥር እርሻ ልማቶቿን በማጎልበት ማችስተር እና ላንክሻየር ለሚገኙ የአልባሳት እና ጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎቿ ጥሬ እቃነት በአስተማማኝ ሁኔታ የማቅረብ ህልም ነበራት። ይህን አካሄዷን ለመግታት ሌላኛው የዚያ ዘመን ተፎካካሪ ፈረንሳይ ጂቡቲ ላይ ሆና መስፋፋት ጀመረች።የፓሪስን መንገድ በኢጣሊያ የመዝጋት የእንግሊዝ ሴራ በኢትዮጵያ እውን ሆነ።

ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ ገባች ። ኢትዮጵያ እና ኢጣሊያ ጦርነት ውስጥ ገቡ በጦርነቱ አዳክሞ ዓባይን መቆጣጠር የእንግሊዝ ከመጋረጃው በስተጀርባ የነበረ እቅድ ነው። ዛሬ ደግሞ ግብፅ ሱዳንን ወደ ኢትዮጵያ ድንበር በመላክ ሁለቱን ሀገራት ጦር ለማማዘዝ እያሰፈሰፈች ነው። መገናኛ ብዙኃኖቻቸው 24 ሰዓታት ስለ ሁለቱ ሀገራት የድንበር ውዝግብ በርዕስ አንቀጽነት እየዘገቡት ነው።ሱዳንም ኢጣሊያንነቷን አጠናክራ የቀጠለች ይመስላል። ያ ኔ ኢጣሊያ የኢትዮጵያን ግዛት ወራ የእኔ ይዞታ ነው በሚል አፍራሽ አካሄድ ስትከተል ነበር። አሁን ደግሞ ሱዳን የኢትዮጵያን ግዛት ወራ እኔ ተወጋሁ እያለች የሴራ አቀነባባሪ ወኪሎቿን ከመጋረጃው በስተጀርባ ሆነው አይዞሽ የሚሏትን ወገኖች ድምፅ እና ድጋፍ ለማግኘት የአዞ እንባ እያባች ነው።

**የሱዳን እና ኢጣሊያ ተመሳስሉ፡-**

ኢጣሊያ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የውሃ ፖለቲካ እና የስትራቴጂክ ቅርምት አፍሪካ ቀንድ ውስጥ የገባችው ገና ሀገረ መንግሥቷ የውህደት ጭቃውን ሳያደርቅ ነበር።ሱዳንም አሁን ላይ እያደረገችው ያለው እንቅስቃሴ ገና የሽግግር የፖለቲካ ትኩሳቷ እና የአልበሽር ዘመን ውልቃቶች ጥሩ ወጌሻ አግኝተው የሱዳናዊያን የምጣኔ ሀብት እድገት ጥያቄ በውል ምላሽ ሳያገኝ ነው። ያኔ እንግሊዝ ኢጣሊያንን ግፊበት እያለች የዲፕሎማሲ ሽፋን ሰጥታታለች። ዛሬም ግብፅ ሱዳንን ግፊበት እያለቻት ነው። የካይሮ ሰዎች ለካርቱም መለዮ ለባሾች በተለይም በአረቡ ዓለም የዲፕሎማሲ ድጋፍ እየሰጧቸው ነው።

የዓድዋ ድል ካርድ እዚህ ላይ መሳብ አለበት።እንዴት እና በምን መንገድ የሚለው ጉዳይ ግን ገና ብዙ ተንታኞችን ፡ምሁራን እና ፖሊሲ አውጪዎችን የሚያነጋግር ቢሆንም የእኔ የምላቸውን የሃሳብ ፍንጣቂዎች በተወሰነ ደረጃ ላቅርብ ።ዋናው ጉዳይ ለውሃ ዲፕሎማሲው መፍትሄ ስትራቴጂ መንደፍ ነው። ማርክ ዜቶን እና ዬሮን ዋረን (2006 _Hydro-hegemony – a framework for analysis of trans –boundary water conflicts) በሚለው ጥናታዊ ስራቸው የውሃ የበላይነት ዲፕሎማሲን ማጠናከር የሚቻለው በሦስት ጉዳዮች ላይ ጠንክሮ በመስራት ነው።አንድም የተፋሰሱን ውሃ ሀብት በብዛት መቆጣጠር፣ሁለትም ከተፋሰሱ አባል ሀገራት ጋር የይስሙላ ትብብር እያደረጉ ታሪካዊ መብትን ማስጠበቅ ሲሰልስ ደግሞ የተፋሰሱ አባል ሀገራት እንዳይጠቀሙ የተለያዩ ዘዴዎችን ገቢር ማድረግ የሚል ነው። ካይሮ አሁን እነዚህን ሦስት ስትራቴጂዎች ገቢር አድርጋለች። ውሃውን በብዛት እየተጠቀመችበት ትገኛለች። ፍትሐዊ በሚል ግን ኢፍትሐዊ አካሄድ ለማንበር ድርድር እያለች በተቃራኒው በወታደራዊ ኃይል ለማስፈራራት እየሞከረች ነው።አዲሱን የጦርነት ስልት የውክልና እና የእጅ አዙር ጦርነትም በሱዳን በኩል እየሞከረች ነው።

የውሃውን እሳት በውሃ የማጥፋት ድህረ ዓድዋ ወታደራዊ ስትራቴጂ፡- በዓለም ላይ ከ286 በላይ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ይገኛሉ። በእነዚህ ወንዞች በርካታ ሀገራት የላይኛው እና የታችኛው ተፋሰስ አባል ሆነው እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። ብዙ ጊዜ በላይኛው ተፋሰስ አባል ሀገራት ግድብ እና ሌሎች የልማት ሥራዎች ሲጀመሩ የታችኞች ተፋሰስ አባል ሀገራት እሮሮ እና እየዬ ዲፕሎማሲያዊ ጩኸታቸውን ያሰማሉ። ሁል ጊዜም መፍትሔ የሚሆነው ግን የተጀመረው ግድብ በድል ሲጠናቀቅ እና ውሃው መፍሰሱን ሲቀጥል ነው። ኢትዮጵያስ ?ኢትዮጵያው ከእነዚያ እንደ አንድ ናት።

የታላቁ ህዳሴ የህዳሴ ግድብን በፍጥነት ማጠናቀቅ አዲሱን የግብፅ ቅኝ ግዛት መንፈስ ለዘለቄታው መስበር ነው። ጥቅሙም ለኢትዮጵያዊያን ብቻ አይደለም። ለሌሎች አፍሪካዊያን ወንድሞቻችን ጭምር እንጂ። ለምን?የዓድዋ ድል ለመላው ጥቁር ሕዝቦች እና አፍሪካዊያን ወንድሞቻችን አይቻል የሚመስለውን የቅኝ ግዛት ቀንበር መስበሪያ ርዕዮት ዓለም ነበር ፓን ኢትዮጵያኒዝም ወደ በኋላ ላይ ፓን አፍሪካኒዝም የተሸጋገረው።

አሁንም የህዳሴው ግድብ ከተጠናቀቀ በሁሉም የናይል ተፋሰስ አባል ሀገራት ግብፅን እንዴት ተቋቁመን እንችላለን ለሚለው የዘመን ግርጃ መቀልበሻ ጥቁር ማቅ ማውለቂያ ሞዴል ነው። ግድቡ ለአፍሪካዊያን ሌላም የምጣኔ ሀብት ሞዴል ይዞ የሚመጣ ነው። እስካሁን በአፍሪካ ግዙፍ ግድቦች በራስ ሀብት ያለ ማንም የውጭ እርዳታ የተገነባ የለም።' የህዳሴው ግድብ ሲጠናቀቅ ይህን የክፍለ ዘመን ግርዶሽ የሚገልጥ ነው። የታላቁ የህዳሴ ግድብ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የዓድዋ ድል ብስራት የፓን ኢትዮጵያኒዝም ርዕዮት ዓለም ግማድ ነው።

ሻሎም ! አሜን።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## «ሞል ኢን አዲስ» - የገበያ አማራጮችን ያቀረበው ቴክኖሎጂ

**አንተነህ ቸሬ**

ቴክኖሎጂ እያንዳንዱን የዓለምን እንቅስቃሴ በተቆጣጠረበት እና ምቹና ቀልጣፋ ኑሮንም ሆነ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን ከቴክኖሎጂው ዘርፍ እድገት ውጪ ማሰብ በማይቻልበት በአሁኑ ወቅት፣ ኢትዮጵያም ከቴክኖሎጂ ዘርፍ እድገት ተቋዳሽ ለመሆን ትልልቅ ተግባራትን እያከናወነች ትገኛለች። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ምርትና አገልግሎትን በዘመናዊ አሰራር የሚያቀርቡ ቴክኖሎጂዎች በብዛት ወደ ሥራ እየገቡ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ አገልግሎት አቅራቢዎችንና ፈላጊዎችን በቀላሉ በማገናኘት ረገድ አሁንም በርካታ መሰናክሎች አሉ።

ለአብነት ያህል በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሞሎች (Malls) የት እና ምን ዓይነት ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎችን እንደያዙ በቀላሉ ማወቅ ፈታኝ ተግባር ሆኖ ይስተዋላል። ለዚህ ችግር በቴክኖሎጂ የታገዘ መፍትሄ የሚሰጥ፣ «ሞል ኢን አዲስ» (Mall in Addis) የተሰኘ ቴክኖሎጂ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ለአገልግሎት በቅቷል። ቴክኖሎጂውን ለአገልግሎት ያበቃው «መልፉን ቴክ» (Melfan Tech) የተባለ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ነው።

«መልፉን ቴክ» በቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ የተሰማራ ድርጅት ሲሆን፣ ሶፍትዌር በማልማት ሥራ (Software Development) ላይ የበለጠ አተኩሮ ይሰራል። ከአምስት ዓመታት በፊት፣ በ2012 ዓ.ም የተመሰረተው ድርጅቱ፣ የብዙ ተቋማትን የንብረት፣ የሰው ሀብት፣ የፋይናንስና ሌሎች የአገልግሎት አሰጣጥና አሰራር ሥርዓቶችን ያዘመኑና ተገልጋዮች (ምርትና አገልግሎት ፈላጊዎች) በፍጥነት እንዲስተናገዱ ያስቻሉ በርካታ ቴክኖሎጂዎችን ሰርቷል።

### የ«ሞል ኢን አዲስ» ምንነትና ፋይዳዎቹ

የ«መልፉን ቴክ» መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ወጣት መልካሙ ምትኩ እንደሚገልጸው፣ «ሞል ኢን አዲስ» (Mall in Addis) በዕለት ከዕለት የስራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለሚገጥሙ ተግዳሮቶች በቴክኖሎጂ የታገዘ መፍትሄ ለመፈለግ እውን የሆነ የቴክኖሎጂ ውጤት ነው። ምርትና አገልግሎት የሚፈልጉ ተገልጋዮች የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት ብዙ መሰናክሎች ያገጥሟቸዋል። ችግሩ የትኞቹ አገልግሎቶች በምን ያህል ብዛት፣ ጥራትና አማራጭ በየትኞቹ ሞሎች ላይ እንደሚገኙ በትክክል ከማወቅ ይጀምራል። ተገልጋዮች የሚፈልጓቸውን ምርቶችንና አገልግሎቶችን የያዙ ሞሎች በተለያዩ የከተማው አካባቢዎች ተበታትነው የሚገኙ ናቸው። በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ሞሎች ተዘዋውሮ ለማዳረስ ደግሞ ብዙ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጭ ይጠይቃል።

ለአብነት ያህል ሰዎች የሚከራይ ቢሮ ሲፈልጉ የትኛው ህንፃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ተለምዷዊ የሆኑትን ሌሎች ሰዎችን የመጠየቅ፣ ማስታወቂያዎችን የመመልከትና የህንፃ ባለቤቶችን እየዞሩ የመጠየቅ አሰራሮችን ይጠቀማሉ። እነዚህ አሰራሮች አድካሚ እንዲሁም ጊዜና ገንዘብ የሚያባክኑ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም አገልግሎት ፈላጊዎችና አቅራቢዎች ባለመገናኘታቸው ምክንያት ያለሥራ የተቀመጡ ቢሮዎች ይኖራሉ። ይህ ደግሞ አከራዮች ማግኘት የሚገባቸውን ዋጋ እንዲሁም ተከራዮችም የሚፈልጉትን ቢሮ ሳያገኙ ብዙ ጊዜያት እንዲያልፉ ምክንያት ይሆናል። በሌላ በኩል ተከራዮች «የስራ ቦታዬ አልታወቀልኝም፣ ብዙ ደንበኛ አላገኘሁም...» በሚሉ ምክንያቶች በየጊዜው የሥራ ቦታቸውን ለመቀየር ይገደዳሉ። አሰሪዎችና ሥራ ፈላጊዎች ደግሞ የሥራ ማስታወቂያዎችን በተገቢው ቦታ የማስቀመጥና የመፈለግ ችግሮች ሲታዩባቸው ይስተዋላል። ስለዚህ ለዚህ ችግር ምላሽ የሚሰጥ በቴክኖሎጂ የታገዘ መፍትሄ ያስፈልጋል። «ሞል ኢን አዲስ» እነዚህንና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን ታሳቢ ያደረገ መፍትሄ ለማቅረብ እውን የሆነ አዲስና ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አማራጭ ነው።

የህንፃ/ክፍሎች ተከራዮች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሥራ ቦታቸውን የሚቀይሩና ሞሎች የተከራዮች መረጃዎች የሚገኙባቸው መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ቴክኖሎጂው ሞሎችን ታሳቢ (Target) አድርጎ የሚሰራ ነው። ይህም ቴክኖሎጂው ሞሎችን፣ ሞሎች ተከራዮቻቸውን እንዲሁም ተከራዮች ደግሞ ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲቆጣጠሩ አመቺ እድል ይፈጥራል። ይህ የሥራ ክፍፍል ቴክኖሎጂው ይበልጥ ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲያገኝ ይረዳል።

በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እንዲሰጥ ይፋ የተደረገው የ«ሞል ኢን አዲስ» ገፅታ፣ ድረ-ገፅ (mallinaddis.com ዌብሳይት) ሲሆን፣ በቀጣይ ደግሞ ለአንድሮይድና ለአይፎን አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችሉ መተግበሪያዎች (Application/App) እየተሰሩ ይገኛሉ፤በቅርቡም ለአገልግሎት ይበቃሉ።

ቴክኖሎጂው የትኛው ሞል ላይ ምን ዓይነት ቢሮዎች፣ ምርቶችና አገልግሎቶች እንዲሁም የሥራ ማስታወቂያዎች እንደሚገኙ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል። በዚህ መሰረት አገልግሎት ፈላጊው ሰው ወደ አካባቢው ይሄዳል። አገልግሎት ፈላጊው የአካባቢውን አቅጣጫ ካላወቀው ቴክኖሎጂው ለዚህ ችግር የሚሆን መፍትሄም አለው፤የቦታውን መገኛ የሚያሳይ አቅጣጫ አመልካች አካትቶ የያዘ በመሆኑ በዚሁ አቅጣጫ አመልካች በመመራት ወደ ስፍራው መድረስ ይችላል።

ተገልጋዮች ወደ ድረ-ገፁ (mallinaddis.com) ሲገቡ ሞሎቹ ምን ያህል ክፍሎች እንዳሏቸው፣ ያልተያዙት ክፍሎቻቸው የትኞቹና ምን ዓይነት እንደሆኑ፣ ምን ያህል የሥራ ማስታወቂያዎች እንዳሉ ... መመልከት ይችላሉ። መረጃዎቹ በጽሑፍ፣ በፎቶና በቪዲዮ የታገዙ ናቸው። ቴክኖሎጂው ለሥራ ማስታወቂያዎች እዚያው ድረ-ገፁ ላይ ወዲያውኑ ማመልከት የሚቻልበትን አሰራርም ይዟል። በሌላ በኩል ለጊዜው ሞሉ ለኪራይ አገልግሎት የሚውል ክፍት ቦታ ከሌለውና ተገልጋዩ በቀጣይ ጊዜ ክፍት ቦታ ሲኖር እንዲያዝለት ከፈለገ፣ ተመዝግቦ እንዲጠብቅ የሚያስችል አሰራርም አለው። ከዚህ በተጨማሪም ቴክኖሎጂው ለአገልግሎት ፈላጊዎች በርካታ አማራጮችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ ከእነዚህ አማራጮች መካከል አንዱ ተገልጋዮች የትኞቹ አካባቢዎች የሚገኙ ሞሎች ላይ አገልግሎት እንደሚፈልጉ ምርጫቸውን የሚያሳውቁበት ዘዴ ነው።

«መልፉን ቴክ» ከሞሎች ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሰረት መረጃዎቻቸውን በከፍተኛ ጥራት ወደ ድረ-ገፁ ያስገባል። የሞል ባለቤቶች የሚሰጣቸውን የተጠቃሚነት መለያ ስም (User Name) እና የይለፍ ቃል (Password) ተጠቅመው ስለሞሎቻቸውና ስለተከራዮቻቸው መረጃዎችን ይመዘግባሉ። ተከራዮችም የሥራ ቦታ ተከራይተው በአከራዮቻቸው ሲመዘገቡ የተጠቃሚነት መለያ ስም እና የይለፍ ቃል ይሰጣቸዋል። ስለምርቶቻቸውና አገልግሎታቸው ዝርዝር መረጃዎችን ያስገባሉ። ከህንፃው ሲለቁ ደግሞ መረጃዎቻቸው ስፍራውን እንዲለቁ ይደረጋል። ወደ ሌሎች ሞሎች ሲዘዋወሩ መረጃዎቻቸውም ወደ አዲሱ የሥራ ቦታዎቻቸው ይዘዋወራሉ፤ይህም አድራሻ ስለመቀየራቸው ያሳውቃል። ምርቶቻቸውና አገልግሎቶቻቸው እንዲተዋወቁላቸው ስለሚፈልጉም መረጃዎቻቸውን አሻሽለው (Update) ለተገልጋዮች ያሳውቃሉ። አዲስ የሚተኩት ተከራዮችም በዚሁ አሰራር መሰረት ይቀጥላሉ።

«መልፉን ቴክ» ቴክኖሎጂው ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ይሆን ዘንድ በርካታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አከናውኗል። ለአብነት ያህልም 130 የሞል ባለቤቶችን፣ ሥራ አስኪያጆችንና ተወካዮችን በመጋበዝ ስለቴክኖሎጂው ምንነትና ፋይዳዎች ሰፊ ገለፃዎችን አድርጓል። በዚህም በርካታ ሞሎች ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ከፍተኛ ፍላጎት ዐሳይተዋል። እስካሁን 24 ሞሎች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ለመመዝገብ ፍላጎታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ።

### የቴክኖሎጂው ልዩ ገጽታዎች

«ሞል ኢን አዲስ» የሞል አስተዳር ስራዎችን ከሚሰሩ ተቋማት ልዩ የሚያደርጉት በርካታ ባህርያትና ገጽታዎች እንዳሉት መልካሙ ያስረዳል። «ሞል ኢን አዲስ» የሞሎች ዝርዝር መረጃዎች ላይ አተኩሮ የሚሰራ አዲስ ቴክኖሎጂ ነው። በተለምዶ ከሚታወቁት የመረጃ ዳይሬክቶሪዎች በእጅጉ የተለየ አማራጭ ነው። በድረ-ገፁ ላይ የሚመዘገቡት መረጃዎች ከጉዳዩ ባለቤቶች በቀጥታ የተገኙ ትክክለኛ መረጃዎች ናቸው። የሥራ ቦታቸውን የሚቀይሩ ተከራዮችን መረጃ በቀላሉ ለማግኘትም ያስችላል።

«በዘርፉ የአሰራር ለውጥ እንዲኖር አድርገናል። የሞሎችን የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን አዘምነነዋል። የሞል አስተዳደር ስርዓቱ (Mall Management) የውስጥ ስራቸውን ያዘምንላቸዋል። በ‹ሞል ኢን አዲ› ቴክኖሎጂ በየጊዜው የታደሰ መረጃ ይቀርባል። ስለሆነም የሞሎቹ ድረ-ገፅ፣ ሞል አስተዳደር (Mall Management) እና ‹ሞል ኢን አዲስ› ተቀናጅተው እንዲሰሩ እድል ይፈጥራል» በማለት ስለቴክኖሎጂው ልዩ ገፅታ ያስረዳል።

ቴክኖሎጂው ለአገልግሎት ፈላጊዎች በርካታ አማራጮችን ያቀርባል። ከእነዚህ አማራጮች መካከል አንዱ ተገልጋዮች የትኞቹ አካባቢዎች የሚገኙ ሞሎች ላይ አገልግሎት እንደሚፈልጉ ምርጫቸውን የሚያሳውቁበት ዘዴ ነው። ቴክኖሎጂው የሞል ባለቤቶችን፣ ተገልጋዮችንና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተዋንያንንና ኅብረተሰብ ክፍሎችን አሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል።

> **ቴክኖሎጂው የሞል ባለቤቶችን፣ ተገልጋዮችንና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተዋንያንንና ኅብረተሰብ ክፍሎችን አሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል**

### ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦው

የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለምጣኔ ሀብት እድገት እጅግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። «ሞል ኢን አዲስ»ም በሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ የራሱ አወንታዊ አሻራ ይኖረዋል። ተጠቃሚው በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ አገልግሎት እንዲያገኝ፣ ጊዜና ገንዘብ እንዲቆጥብ እንዲሁም ስራውን እንዲያቀላጥፍ ያስችለዋል። ተከራዮች የሥራ ቦታ ሲቀይሩ የሞል ሥራ አስኪያጆች በተለምዶ የሚታወቀውን አሰራር (ማስታወቂያ መለጠፍ) መከተል አይጠበቅባቸውም። ደላላዎች በመሐል ገብተው የኪራይን ዋጋ ያለአግባብ እንዳያስወድዱት እድል ይፈጥራል፤ይህ ደግሞ የዋጋ ንረት እንዳይባባስ የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል።

ቴክኖሎጂውን መጠቀም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረጉና የመንገድ መጨናነቅና የነዳጅ ብክነት የሚፈጥሩ አላስፈላጊ ጉዞዎችን ማስቀረት ይቻላል፤በዚህም የነዳጅ ፍጆታን በመቀነስ ለኢኮኖሚው ላይ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ማበርከት ይቻላል። «ሞል ኢን አዲስ» ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚደረገውን ጥረትም ይደግፋል።

### የአገልግሎት ደህንነት ዋስትና

የዘመኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እጅግ የረቀቁና ውስብስብ መሆናቸው፣ የተጠቃሚዎች ሁለገብ የመረጃ አገልግሎት ደህንነት ጉዳይ ትኩረት እንዲያገኝ ምክንያት ሆኗል። «ሞል ኢን አዲስ» ለአገልግሎት ደህንነት ዋስትና የሚሰጡ አሰራሮችን ተግባራዊ ያደረገ ቴክኖሎጂ ነው።

«መልፉን ቴክ» ከዚህ ቀደም በሰናቸው ስራዎች ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (INSA) ጋር በጋራ እንደሰራ የድርጅቱ መስራችና ሥራ አስኪያጅ መልካሙ ይናገራል። የስራዎቹን ደህንነት በተቋሙ ያስፈትሻል። ለፕሮጀክቶች ደህንነት ዋስትና የሚሰጡ ቴክኖሎጂዎችን ይጠቀማል። መረጃዎቹ በከፍተኛ ጥንቃቄና ደህንነት የተመዘገቡ (Encrypted) ስለሆኑ በሌላ ሰው ሊቀየሩና ሊነበቡ አይችሉም። በየጊዜው አዳዲስ ነገሮችን ይጨምራል፤የደህንነት ፍተሻዎችን ያደርጋል። ስለሆነም የቴክኖሎጂው ደህንነት አስተማማኝ ነው።

### ያጋጠሙ ችግሮች

አዲስ ቴክኖሎጂዎችን አበልጽጎ ለአገልግሎት ማብቃት ብዙ ፈተናዎች አሉት። ከእነዚህ ፈተናዎች መካከል አንዱና ዋናው ቴክሎጂውን በብቃት መጠቀምና ተደራሽ ማድረግ የሚችል የሰው ኃይል እጥረት ነው። የብቁ ሰራተኞች ከሥራ መልቀቅም የዚሁ ችግር አካል ነው። «መልፉን ቴክ» ለዚህ ችግር መፍትሄ አድርጎ የተገበረው ተተኪ ሰራተኞችን በትጋት የማፍራትና ተተኪዎችም የባለቤትነት ስሜት ተሰምቷቸው እንዲሰሩ የማድረግ አሰራርን ነው።

### የወደፊት እቅዶች

«ከድርጅቱ ምስረታ ጀምሮ በነበሩት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብዙዎቹ ስራዎቻችን ያተኮሩት ድርጅቱን በማስተዋወቅ፣ ለደንበኞቻችን ታማኝነትን በማሳየትና በመገንባት፣ በፋይናንስ ራሳችንን በማጠናከር ላይ ነበር» የሚለው መልካሙ፤ በአሁኑ ወቅት «መልፉን ቴክ» በተለያየ መልኩ ማደጉንና ብዙ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል አቅም መፍጠሩን ይገልፃል። የድርጅቶችን አሰራር ከማዘመን ወደ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ማበልፀግ ተሸጋግሯል።

«ሞል ኢን አዲስ የአንድ ድርጅት ብቻ አይደለም። ማኅበረሰቡን፣ ድርጅቶችንና ሞሎችን የሚያሳትፍ እንዲሁም በሀገር ደረጃ ትልቅ ፋይዳ ያለው ቴክኖሎጂ ነው። ለብዙ ማኅበረሰብ ተደራሽ መሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ነው። ከደንበኞች ጋር በሚገባ ትስስር በመፍጠር ተከራዮች ምርቶቻቸውን በኦንላይን (Online) መሸጥ የሚችሉበትን አሰራር መፍጠር እንዲሁም ከቪዲዮና ፎቶ በተጨማሪ እጅግ ዘመናዊና የተሻሻሉ የቨርቹዋል ሪያሊቲ እና የሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence - AI) አሰራሮችን እንተገብራለን። ቴክኖሎጂውን ይበልጥ በማዘመንና በማስፋት ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በሌሎች አካባቢዎችም ተደራሽ ለመሆን እናስባለን። ከዚህ በተጨማሪም እንደድርጅት ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን በማበልፀግ ለአገልግሎት የማብቃት እቅድ አለን» በማለት መልካሙ ስለድርጅቱ ቀጣይ እቅዶች ያብራራል። «ሞል ኢን አዲስ» በሚቀጥሉት ስምንት ወራት ከ150 በላይ ሞሎችን ተደራሽ ለማድረግ ያቀደ ሲሆን፣ ደረጃ በደረጃ ሁሉንም የአዲስ አበባ ሞሎች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ ለማድረግ አቅዷል።

ኢትዮጵያ በ2025 «ዲጂታል ኢትዮጵያ»ን እውን ለማድረግ ጥረት እያደረገች እንደምትገኝና በተለያዩ ዘርፎች ላይ ውጤቶች እየተገኙ እንደሆነ የሚገልፀው የ«መልፉን ቴክ» መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ መልካሙ ምትኩ፣ ነው። ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የማድረጉ ጥረት የሁሉንም ዜጋ ርብርብ የሚፈልግ በመሆኑ፣ ኅብረተሰቡ እንደ«ሞል ኢን አዲስ» ያሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲጠቀም እድሎችን ማመቻቸት እንዲሁም ከቴክኖሎጂ ጋር ያለውን ትስስር ማጠናከር እንደሚገባ በአፅንኦት ይመክራል።

# የኢትዮጵያ ሚና ከፓን አፍሪካኒዝም እስከ አፍሪካ ኅብረት እንዴት ይገለጻል ?

እፀገነት አክሊሉ

በቅኝ አገዛዝ ስር የነበሩ የአፍሪካ ሀገራትን ነጻ የማውጣት ዋና ዓላማን አንግቦ በ 32 ነጻ የአፍሪካ ሀገራት የተመሰረተው ድርጅቱ ዛሬ 55 ሀገራትን በአባልነት አቅፏል። ድርጅቱ ከምስረታው ጀምሮ እንደ ደቡብ አፍሪካና ዚምባብዌ ያሉ በቅኝ ግዛት ይማቅቁ ለነበሩ የአፍሪካ ሀገራት ወታደራዊና የስልጠና ድጋፍ ሲሰጥ መቆየቱንም ታሪክ የሚያስታውሰው ነው።

እኤአ በ1960 በአህጉሪቱ 17 ተጨማሪ ሀገራት ከቅኝ አገዛዝ ነጻ መውጣታቸውን ተከትሎም ድሉ በየዓመቱ ግንቦት 25 "የአፍሪካ የነጻነት ቀን" ተብሎ እንዲከበር ምክንያት ሆኗል። አፍሪካን በፖለቲካ በንግድና በምጣኔ ሀብት በማዋሃድ አንድ የተባበረ ሀገረ መንግሥት የመመስረት ውጥንን ያለመው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እነሆ 61 ዓመታትን አስቆጥሯል ።

አብዛኞዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ከምዕራባውያን ቅኝ አገዛዝ ነጻነታቸውን ከተቀዳጁ በኋላ በተለይም "ለአፍሪቃ ነጻነትና ክብር እንቆማለን" ባሉ ሁለት የተለያየ ሃሳብን በሚያቀነቅኑ ቡድኖች የእርስ በእርስ ሽኩቻና ግጭት ሳቢያ አህጉሪቱ በተሻለ መልኩ ጥንካሬና አንድነቷን ጠብቃ ልትቆም አልቻለም ነበር። እንደውም "አፍሪካውያን በፖለቲካና ምጣኔ ሀብት ራሳቸውን ከመቻል ጀምሮ እስከ ኮንፌዴሬሽን አንድ ወደ መሆን ውህደት ሊያመሩ ይገባል" የሚል ዓላማን በሚያራምደው የጋናውን ኩዋሚ ኑኩሩማንና የጊኒውን ሴኩቱሬ የመሳሰሉ የነጻነት ታጋዮችን ያሳተፈው ስድስት ያህል ሀገራት በመሰረቱት የካዛብላንካ ቡድንና " አፍሪቃውያን ራሳቸውን ችለው ለመቆም ምጣኔ ሀብታቸውን ለማሳደግና ጠንካራ እንዲሆኑ ለማስቻል በሌሎች ያደጉ ሀገራት መደገፍ አለባቸው" የሚለውን ሃሳብ በሚያቀነቅነው አብዛኞዎቹ የፈረንሳይ ቅኝ ተገዢ የነበሩ 22 የአፍሪካ ሀገራትን ባካተተው የሞኖሮቪያው ቡድን መሃል የተፈጠረውን ቅራኔን አስወግዶ አንድነትን ፈጥሯል።

መላው አፍሪካውያን ልዩነታቸውን አስወግደው በጋራ የሚሰባሰቡበትንና ወደ ጠንካራ ውህደት የሚያመሩበትን አንድ ወጥ የሆነ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በመመስረቱ ሂደት በዓድዋው የጦርነት ድል ምክንያት በአፍሪካውያንና መላው ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ ከፍተኛ ክብር የተቀዳጀችው ኢትዮጵያ ያበረከተችው ሚና የላቀ መሆኑ በታሪክ ይጠቀሳል።

በ1930ዎቹ ዓ.ም ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ የወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ብቸኛዋ አፍሪካዊት አባል ሀገር እንድትሆን ትልቅ ሚና የተጫወቱት የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዛሬው የአፍሪካ ኅብረት እንዲመሰረት ከሃሳብ ጀምሮ እስከ ተግባራዊ ምስረታው ዕውን መሆን ድረስ እንደ ጋናው ክዋሜ ንክሩማ የኬንያው የነፃነት ታጋይና አርበኛ ጆሞ ኬንያታ የጊኒው ሴኮ ቱሬ የሴኔጋሉ ሊኦፖልድ ሴዳር ሴንጎርና ሌሎችም የአፍሪካ ቀደምት መሪዎች የነጻነት ታጋዮችና የፓን አፍሪካኒዝም ፍልስፍና አቀንቃኞች ጋር በጋራ በመሆን ያበረከቱት አስተዋጽኦ ዛሬም ድረስ ሲወሳ የሚኖር ነው።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ያበረከተችው አስተዋጽኦ ግን ከላይ ከተገለጸውም በላይ የጎላና ታሪካዊ ነበር። ኢትዮጵያ በራስዋ ልጆች ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገር ነች። ኢትዮጵያ ያለምንም የውጭ ኃይል ጥበቃ፣ በራስዋ ልጆች ነጻነቷን አስከብራ መኖሯ፣ ነጻነቷን ለማስከበር ልጆቿ የከፈሉት መስዋእትነት፣ በምእራብ አውሮፓ ሀገራት ቅኝ ግዛት ስር ወድቀው የነበሩ የአፍሪካ ሀገራት ሕዝቦች በራሳቸው አቅም ነጻነታቸውን ለማስመለስ እንዲነሳሱ አድርጓል።

ብዙ የተነገረለት ጥቁር ሕዝቦች የነጭ ወራሪ ኃይልን ያንበረከኩበት የዓድዋ ድል ለዚህ ማሳያነት ይጠቀሳል። የዓድዋ ድል በቅኝ ግዛት ስር ወድቀው የነበሩ የአፍሪካ፣ የኢሲያና የደቡብ አሜሪካ ሕዝቦች የነጻነት ትግል እንዲያቀጣጥሉ አነሳስቷል። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ያበረከተችው አስተዋጽኦ በነጻነት ተምሳሌትነት ተነሳሽነትን በመፍጠር ብቻ የተገደበ አይደለም። በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የአፍሪካ ሀገራት ነጻነታቸውን እንዲቀዳጁ የማድረግ ዓላማ የነበረውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አ.አ.ድ) እንዲመሰረት የመሪነት ሚና ተጫውታለች።

ኢትዮጵያ የተባበረች አፍሪካን ለመመስረት እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረችው ከ1950ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ ሲሆን ፤ በወቅቱ የነበሩትን 30 ገደማ የሚሆኑ ነጻ ሀገራትን በማነሳሳትና የመሪነት ሚና በመጫወት በ1955 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ በአዲስ አበባ አፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት አድርጓል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የመሰረቱት 32 ነጻ የአፍሪካ ሀገራት ነበሩ። ይህ ከሃያ በላይ በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የአፍሪካ ሀገራትን ነጻ ማውጣትና የጥቂት ነጮች የበላይነት ሥርዓት ያለባቸውን ሀገራትም ከዚህ የዘር መድልዎ ሥርዓት ማላቀቅ ዋነኛ ዓላማው ያደረገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በምስረታው ብቻ አላማውን አሳክቷል።

የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ኃይለስላሴ ግንቦት 15 ቀን 1955 ዓ.ም ዋናው የድርጅቱ ምስረታና የአፍሪካ መሪዎች የመክፈቻ ጉባኤ አዲስ አበባ ውስጥ ሲካሄድ ባሰሙት ንግግር "የዚህ ታላቅ ጉባኤ መደረግና የመላው አፍሪካ መሪዎች ተካፋይ መሆን ለዚህች ክፍለ ዓለማችን በውስጧም ለሚገኙ ሕዝቦቻችን ላለን ጥልቅ አሳቢነት ዓይነተኛ ምስክር ነው፤ ተስፋና ራዕያችንንም በተግባር እናሳያለን" በማለት ነበር ጉባኤውን የከፈቱት።

በመጨረሻ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የተቀላቀለችው ሀገር ደቡብ አፍሪካ ስትሆን ደቡብ አፍሪካ የጥቂት ነጮች የዘረኝነት ሥርዓትን አስወግዳ አፍሪካ አንድነት ድርጅትን የተቀላቀለችው በ1986 ዓ.ም ነበር። ታዲያ ይህን የአፍሪካ ሀገራትን ነጻነት ማረጋገጥ ቀዳሚ ዓላማው አድርጎ የተመሰረተና ዓላማውን ያሳካው አፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረትና ተልዕኮውን እንዲወጣ በማድረግ ረገድ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትልቅ ድርሻ ነበራቸው። ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ እንዲሁም ድርጅቱ ዓላማውን በመወጣት ሂደት የጎላ ድርሻ እንዲኖራቸው ያደረጋቸው በቅድሚያ የነጻ ሀገር መሪ መሆናቸው ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት ደግሞ በሕዝቧ መስዋዕትነት የተረጋገጠ ነው።

በ1990 ዎቹ ከግማሽ ክፍለ ዘመን ቆይታ በኋላ አፍሪካ አንድነት ድርጅት ተልዕኮውን አድሶ በአዲስ መልክ መዋቀር ነበረበት። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምዕራፍ ተዘግቶ፣ በ1993 ዓ.ም ግንቦት ላይ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት የሚል ስያሜ ይዞ ዳግም ተመሰረተ። ታዲያ፤ የአፍሪካ ኅብረት በአዲስ የአፍሪካ መጻኢ ራዕይ እንዲፈጠርና ወደ ሥራ እንዲገባ በማድረግ ረገድ ኢትዮጵያ ከአራት አስርት ዓመታት በፊት እንዳደረገችው ሁሉ የጎላ ድርሻ ነበራት።

በወቅቱ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ በዚህ ረገድ ትልቅ ድርሻ ነበራቸው። ኢትዮጵያውያንና ቀደምት የሀገሪቱ መሪዎች ለአፍሪካ ነጻነት ያበረከቱትን ታላቅ አስተዋጽኦ አስታውሰው፤ አዲስ የተመሰረተው የአፍሪካ ኅብረት ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ እንዲሆን ማድረጋቸውም አይዘነጋም። የአፍሪካ ኅብረት ጽህፈት ቤት፣ አዲስ አበባ ላይ እንዲሆን መደረጉ ኢትዮጵያውያንና ቀደምት መሪዎቿ ለአፍሪካ ሀገራት ነጻነት ላበረከቱት አስተዋጽኦ የሚመጥን ተገቢ ዋጋ ነው። ይህንን መነሻ በማድረግ ለኢትዮጵያ መሪ ለኅብረቱ ምስረታ የጀርባ አጥንት ለነበሩት ነጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኅብረቱ ጽህፈት ቤት ቅጥር ጊቢ መታሰቢያ ሃውልት እንዲቆምላቸው ወስኗል። ይህ ኢትዮጵያውያን በመሪዎቻቸው አማካኝነት ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጀምሮ እስካሁን አፍሪካ ኅብረት ድረስ ላበረከቱት አስተዋጽኦ የተሰጠ እውቅና ነው።

በወቅቱ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ያበረከተችው ተኪ የለሽ ሚና አምባሳደር ቆንጂት ስነጊዮርጊስ እንዲህ ያስታውሱታል፤ "አፍሪካ ኅብረት ሲመሰረት ወጣት ዲፕሎማት ነበርኩኝ፤ ውጭ ጉዳይንም በሥራ ከተቀላቀልኩ የስምንት ወር እድሜ ብቻ ነበር ያስቆጠርኩት፤ በዚህ ወጣት እድሜዬ ከ32 ሀገራት መሪዎች ጋር መገናኘት ስሜቱ አስደሳች ነበር" ይላሉ።

እኤአ በ1963 በግንቦት ወር ድርጅቱ ተመሰረተ እዚህ ላይ ለመድረስ ግን የኢትዮጵያ ሚና ላቅ ያለ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያ ባትኖር ድርጅቱ አይቋቋምም ነበር ማለት ይቻላል የሚሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከንጉሥ ኃይለሥላሴ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ በሙሉ ኃይል የተነቃነቁበት እንደነበር ያስታውሳሉ።

ከታሪክ እንደምትረዱት በወቅቱ አፍሪካ ሞኖሮቪያና ካዛብላንካ በሚል በሁለት ተከፍላ የነበረ በመሆኑ ይህንን ሁለት ጎራ አስታርቆ ወደአንድ ማምጣት በጣም ከባድ ስራን ፣ትዕግስትና አልሸነፍ ባይነትን የሚጠየቅ ነበር። ኢትዮጵያውያን ግን በንጉሡ አማካይነት ከባዱን ውጣ ውረድ አልፈው ድርጅቱ እንዲመሰረት ቻርተሩም እንዲፈረም ማድረግ የቻሉበት ከዓድዋ ቀጥሎ ትልቅ ድል የተገኘበት ታሪካችን ነው ይላሉ።

በወቅቱ ከአጼ ኃይለሥላሴ ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ አቶ ከተማ ይፍሩ የነቃ ተሳትፎ በማድረግና ለድርጅቱ መመስረት ዋናዎቹ ተዋናይ ቢሆኑም ኢትዮጵያውያን እገሌ ከእገሌ ሳይባል ሁሉ የተሳተፉበት ነበር ማለት እንደሚቻልም ነው የሚናገሩት።

በተለይም ንጉሡ አጼ ኃይለሥላሴ ስብሰባው እንዲካሄድ የአፍሪካ ኅብረት እንዲመሰረት በየሀገሩ በመዞር አልስማማ ያሉትን በማግባባት ደብዳቤዎችን በመጻፍ ብቻ በጣም በርካታ ሥራዎች ናቸው የተሠሩት፤ መጨረሻ ላይም ሁሉም በመስማማት «እሺ አዲስ አበባ ላይ እንገናኝ» ብለው ወሰኑ በማለት ይናጋራሉ።

በሌላ በኩልም የኢትዮጵያን የሞኖሮቪያና የካዛብላንካውን ረቂቆች ማዋሃድ ነበረባት የሚሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ ይህንን አስታርቆ እንደ ረቂቅ ለማውጣት የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰራተኞች ዳይሬክተሮች ሚኒስትሮች ብቻ ሁሉም ሌት ተቀን ሰርተዋል። ስራውንም አጠናቀው አንድ ረቂቅ አዘጋጁ፤ ስምምነቱም የሚደረግበት ቀን ተቆረጠ ይላሉ ።

ወቅቱ እንደ አሁኑ ሁሉ ነገር የተሟላበት ካለመሆኑ ጋር በተያያዘ ወረቀት የሚባዛው በእጅ ነበር። የ32 ሀገራት መሪዎችን ደህንነት የማስጠበቅ ጉዳይ እና መሪዎቹን በተመቻቹ ሆቴሎች ማሳረፍ ራሱን የቻለ ከባድ ኃላፊነት ነበር ። ከፍተኛ የገንዘብ አቅምን የሚጠይቅ ቢሆንም እኛ ኢትዮጵያውያን ላመንበት ነገር ወደኋላ የምንል ሕዝቦች ስላልሆንን ሁሉንም በአሸናፊነት ተወጥተን የዛሬውን የአፍሪካ አንድነትን እውን ማድረግ ተችሏል።

"ከሁሉም በላይ ከባድ የነበረው ቻርተሩን ማጽደቅ ነበር፤ ለሶስት ቀናት ከተወያዩበት በኋላ በመጨረሻው ቀን ቀኑን ሙሉ ያለእረፍት ዋሉበት፤ ምሽቱም መጣ በዚህን ጊዜ እራት እንብላና ተመልሰን እንምጣ ተባለ። በወቅቱ ግን አጼ ኃይለሥላሴ "እሺ መብላት አለብን ደክሞናል ግን ይችን ቋጭተን እንበላለን" ከማለታቸው ከቤተመንግሥት አስተናጋጆች መጥተው በእያንዳንዱ መሪ ፊት ሰሀን አስቀመጡ። ምግብ ደረደሩ ሃሳባችንን እየበላን እንሂድበት ብለው ንጉሡን አሳመኑ" ይላሉ አምባሳደር ቆንጂት።

ይህ አካሄድ እጅግ በጣም የረቀቀ የዲፕሎማሲ መንገድ ነው የሚሉት አምባሳደር ቆንጂት በወቅቱ እነዛ መሪዎች ለእራት እንውጣ እንዳሉት ቢወጡ አብዛኞቹ እንደማይመለሱ ንጉሱ ገብቷቸው ይህንን ማድረጋቸው የሚያስደንቃቸው ነው። በዛን ምሽትም ሌሊቱን ሙሉ የቀጠለው ስብሰባ ሊነጋጋ ሲል ቻርተሩን በማጽደቅ ተጠናቀቀ በማለት ይናገራሉ።

ኤሚሬት ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በበኩላቸው፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ላይ ሁሉም ሀገራት ተስማምተው የነበረ ቢሆንም ስልቱ ላይ አለመስማማቶች ነበሩ። እንደ እነ ኑኩርማ ያሉት አሁኑኑ አንድ ሀገር እንሁን ሲሉ ኢትዮጵያን ጨምሮ ናይጄሪያ ላይቤሪያ እና ሌሎች ደግሞ መጀመሪያ ኢኮኖሚያዊ አንድነት አግኝተን ነው ወደፖለቲካዊ አንድነት የምንሻገረው የሚል ሃሳብ ያቀነቅኑ ነበር።

እንደ ኤምሬት ፕረሮፌሰር ባህሩ ገላጻ የመጀመሪያው ጉባኤ ሲካሄድ የሞኖሮቪያና ካዛብላንከላ ሃሳቦች ተፋጠው ነበር የመጡት። አጼ ኃይለሥላሴም በተለይም ሴኩ ቱሬን በመጠቀም ኑኩርማ አቋማቸውን እንዲያለዝቡ በማድረግ የአፍሪካ እንድነት ድርጅት ቻርተር ሊፈረም መቻሉን ያስረዳሉ።

"......ሁኔታው አስገራሚ ብሎም ለማሰብ የሚከብድ ነገር ነበር። ሲመጡ ሁለት የተለያዩ ሃሳብ ያነገቡ ሰዎችን አንድ አድርጎ በመሸኘትም ኢትዮጵያና መሪዋ ላቅ ያለ ሚናን በመጫወት ታሪክ የማይዘነጋው ትልቅ ሥራ ሠርተዋል" ይላሉ።

**የ32 ሀገራት መሪዎችን ደህንነት የማስጠበቅ ጉዳይ እና መሪዎቹን በተመቻቹ ሆቴሎች ማሳረፍ ራሱን የቻለ ከባድ ኃላፊነት ነበር። ከፍተኛ የገንዘብ አቅምን የሚጠይቅ ቢሆንም እኛ ኢትዮጵያውያን ላመንበት ነገር ወደኋላ የምንል ሕዝቦች ስላልሆንን ሁሉንም በአሸናፊነት ተወጥተን የዛሬውን የአፍሪካ አንድነትን እውን ማድረግ ተችሏል**

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ‹‹የሴት ልጅ የመሪነት ሚና የሚጀምረው ከቤቷ ነው››

- ወይዘሮ ዘይነብ ሃጂ

**ስምስም መንግሥቱ**



ሴት ልጅ በትምህርት ባትገፋ፣ በሥራም ከፍተኛ በሚባለው የአመራርነት ደረጃ ላይ ባትገኝ የወንዱን ያህል ለምን የሚል ጥያቄ አይነሳም። ይልቁንም ትዳር እስክትይዝ ቤተሰቧን በቤት ውስጥ እንድታግዝ፣ ትዳር ከያዘችም በኋላ ቤተሰቧን እንድትመራ ነው የምትበረታታው። ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ሃይማኖት፣ ባህል እነዚህ ሁሉ ተቋማት ሴት ልጅን በዚህ መንገድ ነው የሚቀርጹት። ብዙዎችም በዚህ ተጽእኖ አልፈዋል።

እንዲህ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ ነገሮችን ለመለወጥ ጊዜ ይወስዳል። ሴት ልጅ ጠንካራ እንድትሆን ጥረት በማድረግ የሚመሰገኑ ቤተሰቦች መኖራቸውና በግላቸውም ተጣጥረው ከወንዶች እኩል አደባባይ የዋሉ በአርአያነት የሚጠቀሱ ሴቶችም እንዳሉ አይዘነጋም ።

ወይዘሮ ዘይነብ ሃጂ አደን ከእነዚህ መካከል ይጠቀሳሉ። ወይዘሮ ዘይነብ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ነው ተወልደው ያደጉት። በአሁኑ ጊዜም በክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። አሁን የሚገኙበት የኃላፊነት ደረጃ ላይ ለመድረስ የበቁት እናትና አባታቸው ለትምህርት ልዩ ቦታ የሚሰጡና የሚያበረታቱ በመሆናቸው፤ እርሳቸውም በመማራቸውና በሥራም ከታች ጀምሮ ጠንክረው በመሥራታቸው እንደሆነ ይገልጻሉ። እንዲማሩ የሚያበረታታ ቤተሰብ ስላላቸውም ያመሰግኗቸዋል። እድለኛ እንደሆኑም ይናገራሉ።

‹‹ሴት ልጅ ተምራ ከወንዱ እኩል በኃላፊነት ቦታ ላይ እንዳትሆን ከፈጣሪ አይደለም የተሰጣት። ሴት ልጅ ወደ ማጀት የሚለው በማህበረሰብ ውስጥ የተፈጠረ ነገር ነው። ›› የሚሉት ወይዘሮ ዘይነብ፤ እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ብዙዎችን እንደጎዳ ይናገራሉ። እንደርሳቸው የቤተሰብ ድጋፍ አግኝተውና በግላቸው ጥረት ማድረግ የቻሉት እጅግ ጥቂት ናቸው ይላሉ። አሁን ላይ ደግሞ ቀደም ካለው በተሻለ ለሴት ልጅ ትኩረት መሰጠቱና በትምህርትም ሆነ በተለያየ የሙያ መስክ ተሰማርተው ባለሙያ በመሆንና በኃላፊነት ደረጃም በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል።

ወይዘሮ ዘይነብ እንደነገሩን፤ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በጅግጅጋ የተለያዩ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው። በርቀት ትምህርት ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ በአስተዳደር ትምህርት ተምረው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመቀጠልም በአግሪካልቸር ኢኮኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ ተመርቀዋል።

የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ ሆነው በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ውስጥ በበጎ ፈቃድ ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ ይሰሩ ነበር። በወቅቱም ቢሮው ለወጣቶች በተለያየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሲሰራ ነበር እርሳቸውም አብረው በበጎ ፈቃድ ሲንቀሳቀሱ ነው የነበረው።

የበጎፈቃድ አገልግሎት ወደ ሥራ ዓለም እንዲገቡም ምክንያት ሆኗቸዋል። እዛው የበጎፈቃድ አገልግሎት በሚሰጡበት ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ውስጥ ባለሙያ ሆነው ተቀጠሩ። ለጥቂት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ደግሞ በሴቶችና ሕፃናት ዘርፍ ውስጥ ተጠባባቂ ኃላፊ ሆነው ተመደቡ። የሴቶችና ሕፃናት ቢሮ ዳይሬክተር ሆነው እንዲሰሩ ኃላፊነት ሲሰጣቸውም ብዙ ጊዜ አልተቆጠረም።

ዳይሬክተር ሆነው በማገልገል ላይ እያሉ ነበር ሀገራዊ ለውጥ የተደረገው። በክልላቸውም አዲስ የአመራርና የሥራ ለውጥ ሲደረግ እየሰሩ በሚገኙበት የሴቶችና ሕፃናት ቢሮ ኃላፊ ሆነው ተሾሙ። ለሶስት ዓመታት ካገለገሉ በኃላ ደግሞ አሁን የሚገኙበት ኃላፊነት ላይ መጡ። ሴት የካቢኔ አባል በመሆንም ብቸኛ ነበሩ።

በካቢኔው ውስጥ ብቸኛ መሆናቸው በአንድ በኩል ለሌሎች አርአያ መሆናቸው ሲያስደስታቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከእርሳቸው ጋር ሌሎች አለመኖራቸው ቁጭት ውስጥ ከቷቸው እንደነበር ይናገራሉ።

በጊዜ ሂደት ግን ለውጥ መጥቶ አሁን ላይ ሴት የካቢኔ አባላት አራት መድረሳቸውን፣ በክልሉ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በምክትል የአመራር ደረጃም የሴቶች ቁጥር ከሁለት የበለጠ እንዳልነበርና አሁን በቁጥር ከ15 በላይ መሆናቸውን ገልጸዋል። የክልሉ አስተዳደር ለሴቶች ያለው ከበሬታም ልዩ ቦታ እንደሚሰጠውና በማህረሰብ አመለካከት ላይም ለውጥ እንዲመጣ መንገድ የከፈተ መሆኑን አስረድተዋል።

ለውጡ የሚበረታታ ቢሆንም በቂ ነው ብለው አያምኑም። እዚህ ላይ የክልሉ አስተዳደር ሴቶች እንዲበረታቱ፣ ቅድሚያም ሰጥቶ እየሰራ እንደሆነም አመልክተዋል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ሲመጡም ሴቶች ወደ ኃላፊነት እንዲመጡ እንደሚበረታቱና ሃምሳ ሃምሳ ለማድረስም እንደሚሰራ የተናገሩትንም አስታውሰዋል።

ወይዘሮ ዘይነብ ሴቷ የችሎታ ማነስ ኖሯት ነው ብለው አያምኑም። ‹‹ ወንዱ ሴት ልጁ ትልቅ ቦታ እንድትደርስ ፍላጎትና ምኞት አለው። በጎሳም እንዲሁ ሴት ልጅ መበረታታት አለባት ይባላል። ተግባር ላይ ግን አያውሉም›› ነው ያሉት። ሕገመንግሥቱም ለሴቶች መብቱን ቢሰጥም ተግባራዊነቱ ላይ ክፍተት መኖሩን ነው የገለጹት።

ወይዘሮ ዘይነብ እንዳሉት፤ የሴት ልጅ የመሪነት ሚና የሚጀምረው ከቤቷ ነው። በሥነ ምግባር የታነጹ፣ ሀገርን የሚጠቅሙ ጥሩ ዜጎችን በማፍራት ረገድ ትልቁን ድርሻ የምትወስደው ሴት ናት። ቤት የማስተዳደሩም ሚና ከወንዱ ድርሻ ከፍ ያለ ነው። በቤት ውስጥ የምትወጣው ኃላፊነት ለሥራ ዓለምም ትልቅ ተሞክሮ ሊሆን እንደሚችል ያምናሉ። የራሳቸውን ተሞክሮም ለአብነት ያነሳሉ።

‹‹ትዳር መሥርቻለሁ። ልጆችም አሉኝ። በቤት ውስጥ የሚጠበቅብኝንና የእናትነት ድርሻዬን እየተወጣሁ ትዳሬን ሳላጎድል በሥራ ኃላፊነቴም ክፍተት ሳልፈጥር እየተወጣሁ ነው›› ሲሉ አስረድተዋል። ሴት ልጅ በሥራ ላይ ኃላፊነቷን በታማኝነት ለመወጣትም ትጉህ እንደሆነች፣ በሀብት አጠቃቀምም ቢሆንም ጠንቃቃና ብክነትን እንደምትከላከል ይገልጻሉ።

ወይዘሮ ዘይነብ በአንድ ወቅት ለሥልጠና ኔዘርላንድ ሄደው በነበረበት ወቅት የታዘቡትንና ተሞክሮም ይሆናል ብለው ያመኑበትንም እንዲህ አካፍለዋል። እርሳቸው እንዳሉት፤ በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች ሲጎበኙ ሴቶች በተለያየ የሥራ ዘርፍ ውስጥ ይገኛሉ። በአመራርነት ደረጃም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ሴቶች ናቸው። የፓርላማ አፈ ጉባኤዋም ሴት ናት። ሴቶች በኃላፊነት ደረጃም ሆነ በተለያየ የሥራ ዘርፍ ውስጥ እንዲገኙ የተደረገው በብቃታቸው እንደሆነም በቆይታቸው ለመገንዘብ ችለዋል።

ወይዘሮ ዘይነብ ሀገሪቱ የደረሰችበትን የእድገት ደረጃም ነበር ያደነቁት። እርሳቸው እንዳሉት ሀገሪቱ ውሃ ላይ ነው የተመሰረተችው ማለት ይቻላል። ቤቶች የተገነቡት በውሃ ላይ ነው። በግንባታ ሥራውም የሴቶች ተሳትፎ እጅግ ከፍተኛ እንደነበር ተነግሯቸዋል። በርግጥ ሴቶቹ ጠንክረው ለመውጣታቸው ምክንያት ነበር። በጦርነት ምክንያት የወንዱን ድርሻ ተክተው የሚሰሩት ሴቶች ነበሩ። ‹‹ሀገራችንን ሴቶች ናቸው የገነቡልን›› የሚል እውቅናና አክብሮትም እንደተሰጣቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ዘይነብ መንፈሳዊ ቅናትም አድሮባቸዋል።

ኔዘርላድን እንዲህ በማሳያ ለመግለጽ ቢሞክሩም፤ ብዙ በጥንካሬያቸው የሚጠቀሱ ኢትዮጵያውያን ሴቶች መኖራቸውን ይገልጻሉ። ወንዶች ይህን እንደሚያምኑም ይጠቅሳሉ። ሆኖም ግን ሴት ወደ አመራርነት እንድትመጣ ፍላጎት ያለው ወንድ አነስተኛ እንደሆነ ይናገራሉ።

ወይዘሮ ዘይነብ እንደሚሉት እርሳቸውም በግላቸው ሴቶች የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ከፍተኛ ፍላጎት ስላላቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በምክርም ሆነ በሚችሉት ሁሉ ለማገዝ ዝግጁ ናቸው። ይህንን የሚገነዘቡ አንዳንዶችም ‹‹ ሌላ ተቋም እየመራሽ አሁንም ስለሴቶች ታወሪያለሽ ›› ይሏቸዋል። እርሳቸውም መልሳቸው አንድና አንድ ‹‹ያገባኛል›› ነው። ሥራቸው በሴቶች ዘርፍ ውስጥ ባይሆንም እንደሚመለከታቸው ያምናሉ።

ወይዘሮ ዘይነብ እንዳሉት ዛሬ ወደ ከተማ የመምጣት እድል በመኖሩ በገጠር የሚኖሩ ሴቶች የከተማውን አኗኗር በማየት እራሳቸውን በኑሮ ለመለወጥ በተለያየ ነገር ላይ ሲሳተፉና ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል። በተለይ ደግሞ የተንቀሳቃሽ ስልክ ለገጠሩ የህብረተሰብ ክፍልም ተደራሽ መሆኑ ለሴቶች ንቃተ ህሊና ከፍ ማለት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህም ለውጦች እየታዩ ቢሆንም ለውጥ አለ ብለን መዘናጋት የለብንም።

ከከተማ በጣም ርቀው የሚገኙ ከመረጃ በመራቃቸውና ለውጥ ለማድረግም ዕድሉን ባለማግኘታቸው ዛሬም ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ከመጋለጥ አልዳኑም። እዚህ አካባቢ መድረስ አለብን። ለውጥ መጣ ማለት የሚቻለውም ለውጡ ሀገራዊ መሆን ሲችል ነው።

ወይዘሮ ዘይነብ በአመራርነት ላይ የገጠማቸው ነገር ይኖር እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ሰውንና ሥራን መምራት ከባድ ነው። ለትልቁም ለትንሹም ነገር መቆጣት ሳይሆን፤ በትእግስትና በጥበብ ነገሮችን ለመፍታት መሞከር የሚል መርህ ስላላቸው በዚህ መንገድ ነው የሚጠቀሙት።

ከእናትነት ጋርም ያያይዙታል። እናት በባህሪ ወጣ ያለውንም፣ ጥሩ ሥነምግባር ያለውንም ልጆችዋን እኩል እንደምትወድና በባህሪ ወጣ ያለውን ለመመለስ የተለያየ ጥረት እንደምታደርግም በመግለጽ፤ በሥራ ኃላፊነታቸው ላይም እንዲህ ያለው ነገር ሲገጥማቸው በሥራቸው ያሉትንም ሰራተኞች እንደልጆቻቸው አይተው ነገሮችን ለማስተካከል ጥረት እንደሚያደርጉ ነው ያስረዱት።

ነገሮች ከአቅም በላይ ሆነው ሲያገኟቸውም በችኮላ ከመወሰን ይልቅ ጊዜ ሰጥቶ ማጤንን ይመርጣሉ። በተፈጥሮአቸውም ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ቶሎ ውሳኔ ለመስጠት የመቸኮል ባህሪ እንደሌላቸውና በሥራ ላይ መቆየታቸውም ነገሮችን ለማመዛዘን አስችሏቸዋል። ኃላፊነታቸውን ሲወጡም ቢሮ በር ዘግተው ፀሐፊ እያዘዙ የሚሰሩ ሳይሆኑ፤ በሥራቸው ያሉ ሰራተኞች ቢሮ በመሄድና እርሳቸው ጋርም በማስጠራት ስለ ሥራቸው ከእነርሱም ሃሳብ በመውሰድ አሳታፊ በሆነ ሁኔታ ሰርተው ለማሰራት ጥረት እንደሚያደርጉ ነው የነገሩን።

ተስፋ መቁረጥ የሚባል ነገር በእርሳቸው በኩል ተቀባይነት የለውም። ‹‹ተስፋ ከቆረጥኩ እስከዛሬ የሰራሁት ሁሉ ዋጋ አጣ ማለት ነው። ዜሮ ሆንኩ። ይሄ ሽንፈት ነው። የበለጠ ጠንክሬ ኃላፊነቴን መወጣት እንጂ መሸነፍ የለብኝም›› ሲሉም ምላሽ ሰጥተዋል።

ወይዘሮ ዘይነብ ወደ ኃላፊነት የመጡት ሥራን ከታች ተለማምደው ነው። ከታችኛው እርከን ጀምሮ ወደላይ መውጣት ስላለው ጠቀሜታም እንደገለጹት፤ ሥራን ከታች መጀመር በተለያየ ነገር ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለመያዝ እንደሚያግዝና ወደ ኃላፊነት ከተመጣ በኋላም ኃላፊነትን በቀላሉ ለመወጣት እንደሚጠቅም ነው ያስረዱት።

ሴት አመራሮችን እንደብርቅ የምናይበት ጊዜ እየተለወጠና ከቀደሙት ዓመታትም ለውጦች ቢታዩም፤ በከፍተኛ አመራርነት ላይ የሚገኙት ሴቶች ቁጥር አሁንም የሚፈለገውን ያህል ነው ለማለት አያስደፍርም።

**በሥነ ምግባር የታነጹ፣ ሀገርን የሚጠቅሙ ጥሩ ዜጎችን በማፍራት ረገድ ትልቁን ድርሻ የምትወስደው ሴት ናት**

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**የዛሬው አዲስ ዘመን ወደ 1969 ዓ.ም ይወስደናል። ወንጀል ማኅበራዊና ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ያስቃኘናል። ያስምንም ምክንያት በእብሪት ተነሳስቶ በአንድ ጀንበር ሦስት ሰዎችን የገደለው ወንጀለኛ፤ በአንድ ሰዓት ብቻ አንድ ሺህ 649 ሰዎችን ጢም የላጨው ግለሰብ፤ እንዲሁም አደንና አዳኝ እንስሳቱ እንዴትስ አለቁ የሚሉ ጉዳዮችን ከትዝታ ማኅደራችን መዘን አቅርበናል።**

**በእብሪት ሦስት ሰዎች የገደለው ተፈረደበት**

በእብሪተኝነትና በጥጋበኝነት ተነሳስቶ የሁለት ሰዎች ሕይወት ካጠፋ በኋላ ተሰውሮ በውንብድና ሲኖር የነበረውና በዚህም ወቅት የአንድ ሠላማዊ ሰው አጥርና የከብት መኖ አቃጥሎ፤ ግለሰቡንም ከእንቅልፉ ቀስቅሶ በጥይት የገደለው ጀፍላ ደገፉ ሕዝብ በተሰበሰበበት በገበያ ቀን በስቅላት በሞት እንዲቀጣ በቅርቡ ያስቻለው የሸዋ ክፍለ ሀገር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወሰነ።

...

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ሲሰማና ሲመረምር፤ ሟቾቹ ዘውዴ ሩፌና ከተማ ዘውዴ ከለቅሶ ሲመለሱ አንድ ቤት ገብተው ከሌሎች ሰዎች ጋር ሆነው አረቄ ሲጠጡ ጀፍላ ደገፉም እዚያ ቤት ሄዶ ዘውዴ ሩፌን የገዛችሁትን አረቄ ልጠጣ ሲላቸው መከልከላቸውንና እሱም "ይህ ጠብመንጃ ነገ ሴራ ሚካኤል ያመጣችኋል" ብሎ መውጣቱንና እነርሱ ከወጡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጥይት ድምፅ መሰማቱን ምስክሮች ለዐቃቤ ሕግ በሰጡት ቃል ተረድቷል።

...

በውንብድና በሚኖርበት ጊዜ ቱጃር ደምሴን በመግደሉና በአጠቃላይ የሦስት ንጹሐን ዜጎችን ደም ማፍሰሱ ልማድ ያደረገ በክፉ ፍላጎትና በጨካኝነት የተነሳሳ ልማደኛ ወንጀለኛ ሆኖ ማግኘቱንም ፍርድ ቤቱ ገልጧል።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 29 ቀን 1969 ዓ.ም)**

**በአንድ ሰዓት -በአንድ ሰው እጅ የሺህ 649 ሰዎች ጢም ተላጨ**

የዘር ሐረጉም ሀገረ ትውልዱ ከወደ እንግሊዝ እንደሆነ የሚነገርለት ሚስተር ዲኒ ሮው ባለፈው ወር አጋማሽ ላይ የአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠኝ ሰዎች ጉንጭና አገጭ ላይ የተከመረ ጢም በአንዲት ሰዓት ውስጥ ሙልጭ አድርጎ እየላጨ፤ ብርቱካን በማስመሰል የምድራችን ቁንጮ ጢም ላጭ ለመባል በቅቷል።

....

ጠጉርን በባልጩት ቀስ በቀስም በምላጭ እየተሸለተ የኖረው የሀገሬ ሰው ከዘመን አመጣሾች መቀሰኛና "ክሊፐርና ሸቨር" መተዋወቅ የጀመረው መቼ እንደሆነ በትክክል አላውቅም።

....

ካቻምና ደሴ ከተማ ስለሚገኙት ፀጉር አስተካካይ ሴት ወይዘሮ በጻፍኩ ጊዜ ሌላም ቦታ የወንዶችን ፀጉር የሚያስተካክሉ ሴቶች ካሉ ጻፉልኝ ብዬ ነበር። ስለሌሉ ነው መሰለኝ ምላሽ አላገኘሁም። ባሕር ማዶ ሴቶች የወንዶችን ፀጉርና ጢም በማስተካከል ሞቅ ያለ ገበያ ያገኛሉ። ታዲያ ሴቱ ሁሉ ከመሬት እየተነሣ መቀስና ምላጭ አንጠልጥሎ "ዘመናዊ" ጠጉር አስተካካይ ነኝ የሚል እንዳይመስላችሁና አደራ።

**(አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 5 ቀን 1967 ዓ.ም)**

**በደስታ በሽታ ቁጥጥር ላይ ሴሚናር ተጀመረ**

የማዕከላዊ ቀጠና ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት የዳልጋ ከብቶችን ጤንነት ለመንከባከብና የደስታ በሽታን ከክልሉ ለማጥፋት እንዲቻል ያዘጋጀው ሴሚናር መስከረም 12 ቀን 1969 ዓ.ም ተጀምሯል።

....

ጓድ መስፍን በዚሁ ጊዜ ባደረጉት ንግግር ለዳልጋ ከብቶች ሕይወት አስጊ የሆነውን የደስታ በሽታ ከአፍሪካ ምድር ለማጥፋት በሚደረገው ጥረት መሠረት በኢትዮጵያም ይኸው ተመሳሳይ እንቅስቃሴ በተጠናከረ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል።

**(አዲስ ዘመን መስከረም 15 ቀን 1969ዓ.ም)**

**አደንና አዳኝ**

ምንም እንኳን በሀገራችን በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በሌላው ዓለም ውስጥ የሌሉ በጣም ብርቅዬ የሆኑ የዱር እንስሳት ቢገኙም፤ ከጥንቱ ጋር ሲወዳደር ግን በቁጥርም ሆነ በዓይነት በጣም አናሳ መሆናቸው በተለያዩ ጊዜያት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ተገልጿል። ለዚህም የዱር እንስሳት ቁጥር እያሽቆለቆለ ለመምጣቱ ሰበብ ኋላ ቀር ልማድና ወግ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ለአብነት ያህል የሚከተለውን እንመልከት።

- ዝሆን ገዳይ_ አዳኙ 30 ሰው እንደገደለ ይቆጠርለታል።
- አውራሪስ ገዳይ_ አዳኙ 15 ሰው እንደገደለ ይቆጠርለታል።
- አንበሳ ገዳይ _ አዳኙ 5 ሰው እንደገደለ ይቆጠርለታል።
- ቀጭኔ ገዳይ_ የቀጭኔ ገዳይ ሚስት በውሀ መቅዳት ቅድሚያ ይሰጣታል።
- ግሥላ ገዳይ_ ግሥላ ገዳይ ሳይፎክር ቀድሞ የሚነሣ የለም።
- ተኩላ ገዳይ_ ሌሎች ገዳዮች እየፎከሩ ሳሉ ተኩላ ገዳይ ቢነሣ ሁሉም ዝም ይላል።
- ነብር ገዳይ_ ነብር እሱው አጥር ግቢ ገብቶ ሴት ገደለችው የሚል ንግርት ስላለ ገዳዩ ለ15 ቀን ብቻ ቂቤ ይቀባል።

(ከዝክረ ነገር የተወሰደ)

**(አዲስ ዘመን መስከረም 9 ቀን 1968 ዓ.ም)**

**"ጠራርግና ፕላስተር ለጥፍለት"**

በሐረርጌ ክ/ ሀገር በወበራ አውራጃ በሜታ ወረዳ በጨለንቆ ከተማ የሚገኘው አንድ ጤና ጣቢያ (ክሊኒክ) ቀድሞ በአንድ ባለሙያ ቅን አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሲሆን ዛሬ ሁለት ባለሙያዎች ተመድበውለት ይገኛል።

...

ሕመምተኛውን እያዩ እንዳላዩ በመሆን ከአንዳንድ ቦዘኔዎች ጋር አብዛኛውን የሥራ ጊዜ በዋልጌነት ሲያሳልፉ ይታያሉ።

ለዚህ አስተያየት መነሻ የሆነን ግን ባሁኑ ጊዜ ይባስ ብለው፤ የመርፌ መውጋቱን ተግባር አልጀመሩም እንደሆን እንጂ ቁስል ነክ የሆነ ታማሚ ሲመጣ "ጠራርግና ፕላስተር ለጥፍለት" በማለት ለጤና ጣቢያው ዘበኛ ትዕዛዝ በመስጠትና እነሱ በዋልጌነታቸው በመቀጠል ምንም ሙያ የሌለው ዘበኛ ሐኪም መሆኑ ነው። ይህ በማናለብኝነት ፈሩን የለቀቀ አሠራር ቀጥሎ በሕይወት ላይ ሌላ ጉዳት ከማድረሱ በፊት የሚመለከተው ክፍል አንድ ይበልልን።

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 4 ቀን 1969 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## እስራኤል ራፋህ ላይ ጥቃት ልትፈጽም እንደምትችል አስጠነቀቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ራፋህ ከተማ

ሐማስ በጋዛ የታገቱ ሁሉንም እስራኤላውያን ካለቀቀ መጋቢት 1 ቀን 2016 ዓ.ም በራፋህ ላይ የምድር ጥቃት እንደሚከፈት የእስራኤል የጦር ካቢኔ አባል ቤኒ ጋንትዝ አስጠነቀቁ።

እስራኤል በጋዛ በተፈናቃዮች በተጨናነቀችው ደቡባዊቷ ከተማ ራፋህ ወታደሮቿ ሊገቡ እንደሚችሉ ስትገልጽ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

ሆኖም እስራኤል አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆኑ ፍልስጤማውያን በተጠለሉባት ራፋህ ላይ ለመፈፀም ያቀደችው ጥቃት ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተቃውሞ ገጥሞታል።

ቀደም ብሎ የተባበሩት መንግሥታት የኀብረተሰብ ጤና ኤጀንሲ እንደገለጸው እስራኤል በፈፀመችው ጥቃት በጋዛ የሚገኘው ዋና ሆስፒታል ሥራ ማቆሙ ተጠቁሟል።

የዓለም ጤና ድርጅትም በሆስፒታሉ ያለውን ሁኔታ ለመገምገም በሰሜን ራፋህ፣ ኻን ዮኒስ ከተማ በሚገኘው ናስር ሆስፒታል ለመግባት እንዳልተፈቀደለት ገልጿል።

የእስራኤል መከላከያ ኃይል በሐማስ ታግተው የተወሰዱ እስራኤላውያን በሆስፒታሉ ውስጥ እንደሚገኙ የደኅነንት መረጃዎቼ አመልክተዋል በማለት ወደ ሆስፒታሉ በመግባት ጥቃት የከፈተው ያለፈው ሐሙስ ዕለት ነበር።

መከላከያ ኃይሉ ሐማስ "ሆስፒታሉን ለሽብር ተግባር ተጠቅሞባታል" ሲል በመክሰስ በናስር ሆስፒታል ላይ የከፈተውን ዘመቻ "ትክክለኛ እና ውስን" ሲል ገልጾታል።

የቀድሞው የመከላከያ ሚኒስትር ጋንትዝ ያለፈው እሑድ ዕለት ሲናገሩ "በረመዳን ፆም መጀመሪያ ታጋቾቻችን ወደ ቤታቸው ካልገቡ ራፋህን ጨምሮ በሁሉም ቦታዎች ውጊያው እንደሚቀጥል ዓለምም ሆነ የሐማስ መሪዎች ሊያውቁ ይገባል" ብለዋል።

የቀድሞው ሚኒስትሩ ጨምረውም እስራኤል በሠላማዊ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ከአሜሪካ እና ከግብፅ አጋሮቿ ጋር በመነጋገር የሚወጡበትን ሁኔታ በተቀናጀ ሁኔታ ታመቻቻለች ብለዋል።

ጋንትዝ ሠላማዊ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ከግብፅ ጋር እንደሚሠሩ መግለጻቸው እስራኤል የተወሰኑ ፍልስጤማውያን ከጋዛ ሰርጥ በመውጣት ከፍተኛ ግንባታ እየተካሄደበት ነው በተባለው የግብፅ ድንበር ላይ እንዲጠለሉ ትጠብቃለች የሚለውን መረጃ እንደሚያጠናክር ቢቢሲ ዘግቧል።

ነገር ግን የእስራኤል ባለሥልጣናት ሠላማዊ ሰዎችን ከአካባቢው ስለሚያስወጡበት ዕቅድ በዝርዝር አልገለጹም ብሏል።

የእስራኤል የጦር ካቢኔ ከፍተኛ የፀጥታ ባለሥልጣናትን የያዘ ሲሆን በሐማስ የተመራው ታጣቂ ቡድን ጥቅምት ወር ላይ ሐማስ ከፈጸመው ጥቃት በኋላ የተቋቋመ ነው።

እስራኤል ሐማስ 130 የሚሆኑ እስራኤላውያንን በጋዛ አግቶ ይዟል ብላ ታምናለች። ከራፋህ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ጥቂት ሰዎች አካባቢውን ለቀው ወደ ባሕር ዳርቻው እየወጡ ሲሆን አብዛኞቹ ደግሞ የሚያደርጉት ቸግሯቸው እዚያው እየጠበቁ ይገኛሉ።

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጫና ቢያሳድርም የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታንያሁ የሐማስ ታጣቂዎችን ለማጥፋት በራፋህ ላይ የምድር ጥቃት እንደሚከፍቱ ዝተዋል።

ግብፅ እና ሌሎች የዓረብ ሀገራት እስራኤል በራፋህ ላይ የምትፈፅመው ጥቃት በርካታ ፍልስጤማውያን ወደ ግብፅ እንዲሰደዱ ይገፋፋል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

ሳዑዲ ዓረቢያ ራፋህ ላይ ጥቃት የሚፈፀም ከሆነ ከፍተኛ ቀውስ እንደሚያስከትል ጥርጥር እንደሌላት ገልጻለች።

በመሆኑም እስራኤል በራፋህ ላይ ለመፈፀም ካቀደችው ጥቃት እንድትታቀብ በርካታ ሀገራት ጥሪ እያቀረቡ ነው።

እስራኤል ከጥቅምት ወር ጀምሮ የጋዛ ሰርጥን ወደ ፍርስራሽነት የቀየረውን ጥቃት አድርሳለች። ጦርነቱ ከጀመረ አንስቶም በአብዛኛው ሕጻናት እና ሴቶች መገደላቸውን በሐማስ የሚመራው የጤና ሚኒስቴር አስታውቋል።

በጋዛ የሚካሄደው ውጊያ ቢቀጥልም በእስራኤል እና በሐማስ መካከል የተኩስ አቁም እንዲደረስ የሚደረገው ጥረት ሰሞኑን በካይሮ እየተካሄደ ነው።

ኔታንያሁም በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የቀረበላቸውን ጥያቄ ተከትሎ ተደራዳሪዎችን መላካቸውን ገልጸው፣ የሐማስ ፍላጎት የማይጨበጥ ነው በማለት ተደራዳሪዎቻቸው የደረሱበትን ይዘው እስካሁን አለመመለሳቸውን ተናግረዋል።

ሐማስ በበኩሉ የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ላለመደረሱ እስራኤልን ተጠያቂ እያደረገ ይገኛል።

# ስፖርት





## ሀገር አቀፍ የስፖርት የጸረ-አበረታች ቅመሞች ንቅናቄ ይካሄዳል

**ብርሃን ፈይሳ**

የየትኛውም ስፖርት ጸር የሆነው የስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት(ዶፒንግ) በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ከነበረው በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋና ታዋቂ አትሌቶችንም ጭምር እየጎዳ ይገኛል። ይህንን ተከትሎም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጉዳዩ ከአቅሙ በላይ መሆኑንና ስፖርቱን በበላይነት እየመራ ባለው ተቋም ድጋፍ እንዲደረግለት መጠየቁን ተከትሎ የንቅናቄ መድረክ ተዘጋጅቷል።

በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር፣ የኢትዮጵያ ጸረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን እንዲሁም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በጋራ በተዘጋጀው በዚህ ሀገር አቀፍ የምክክርና የንቅናቄ መድረክ ላይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተካፋይ እንደሚሆኑ ታውቋል።

በተለያዩ ዓለማት ላይ በሚካሄዱ የአትሌቲክስ ውድድሮች ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በበላይነት በማጠናቀቅ ትልቅ ስምና ዝና እንዳላቸው ይታወቃል። ያም ሆኖ ከአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ጋር በተያያዘ በሚደረጉ ምርመራዎች በዚህ ቅሌት ውስጥ የሚገኙ አትሌቶች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እያሻቀበ ይገኛል። ይህ ሁኔታም በጸረ አበረታች መድኃኒቶች ባለስልጣኑና ፌዴሬሽኑ አቅም ብቻ የማይገታ በመሆኑ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ጉዳዩን በሚመለከት በከፍተኛ ትምህርት ባለሙያዎች ጥናታዊ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ከቀናት በኋላ በሚደረገው የንቅናቄና የምክክር መድረክ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ለተግባራዊነት ወደ ሥራ እንደሚገባም ነው የተጠቆመው።



ኢትዮጵያ መልካም ገጽታዋን ከገነባችባቸው ዘርፎች መካከል ቀዳሚ በሆነው አትሌቲክስ በላብና በጥረታቸው ውጤታማ የሆኑ አትሌቶችን ታሪክ የሚያጎድፍ እንዲህ አይነት ችግር እየተስፋፋ መምጣቱ እንደ ሀገርም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል።

በመሆኑም በምክክር መድረኩ ላይ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው የአትሌቲክስ ባለሙያዎች ባለፈ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የጤና ሚኒስትር፣ ትምህርት ሚኒስትር፣ የፍትህ አካላት፣ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ወዘተ ተካፋይ እንደሚሆኑ በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ ገልጸዋል።

አበረታች ቅመሞችን በሚመለከት ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በተገበረቻቸው ጠንካራ ሥራዎች ለሌሎች ሀገራት አርዓያ በመሆን ተሞክሮዋን ስታካፍል ቆይታለች። ይሁን እንጂ አሳሳቢው የዶፒንግ ተጠቃሚነት ጉዳይ በኢትዮጵያ መጨመሩ በተደጋጋሚ ተነስቷል። ይህንን ተከትሎም የሀገሪቱን ስፖርት በበላይነት የሚመራው የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባር ለተቆጣጣሪው አካል ድጋፍ መስጠትና ክትትል ማድረግ መሆኑን ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

ዶፒንግን ለመቆጣጠር እንደ አፍሪካ ጠንካራ ሥራ ተከናውኗል፣ ነገር ግን ጉዳዩ ብዙ መልክ ያለው በመሆኑ ሊሰፋ ችሏል። በተለይም ከባለስልጣኑ ተግባር ጎን ለጎን የሕግ አካሉ እገዛ አናሳ መሆኑ ተመላክቷል። የፍትህ አካላት በጉዳዩ ላይ ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው እንዲሁም የወንጀል ሕጉ በምን መልኩ ይፈጸማል የሚለውም በውይይት መድረኩ ትኩረት የሚያገኝ ጉዳይ ነው።

ከዚህ ቀደም መሰል ጉዳዮች ላይ የመዘናጋትና ረጅም ጊዜ በመውሰድ መፍትሄ ሳይገኝ የተረሳበት ሁኔታ መፈጠሩን ተከትሎም የሕግ አካላት በተዘጋጀው ጥናት ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

በስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት መስፋፋት ምክንያት የሚሆኑ በርካታ ጉዳዮችን ማንሳት ቢቻልም በተለይ አሰልጣኞች ከውጪ ሀገራት ጭምር በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ይስተዋላል። በመሆኑም የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ይህንን በሚመለከት እንዲሳተፍ ተደርጓል። የመድኃኒት መደብሮችም ከችግሩ ምንጮች መካከል የሚካተቱ መሆኑን ከዚህ ቀደም የተከሰቱ ጉዳዮች ማሳያ ናቸው። በግል የሚሰለጥኑ አትሌቶች መብዛትን ተከትሎ የማናጀሮች ቁጥር ቢያሻቅብም መሰል መርሀ ግብሮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ ግን አናሳ ነው። በመሆኑም በዚህ መድረክ ማናጀሮች በዋናነት ተሳታፊ ይሆናሉ።

በስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት በአስከፊ ሁኔታ ተዘፍቆ የቆየው የኬንያ አትሌቲክስ እየቀነሰ የመጣበት ተሞክሮም በጥናቱ እንዲካተት ተደርጓል። ተሞክሮውን መነሻ በማድረግም የተሻለ ሥራ ለማከናወን በማቀድ ንቅናቄው ይካሄዳል። በቀጣይም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራው በስፋት ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ችግሩ ሲፈጸም ደግሞ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። ነገር ግን ከታዳጊዎች አንስቶ ስለ ስፖርት አበረታች ቅመሞች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር በሥርዓተ ትምህርት አካቶ ጠንካራ ዕውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል።

የመገናኛ ብዙኃንም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለሕዝቡ ግንባቤ ለማስጨበጥ እንዲተጉ ሥራ አስፈጻሚው መልዕክት አስተላልፈዋል።

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ግሩም ተስፋዬ ወ/ዮሃንስ የሰሌዳ ቁጥር 02-52573 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር MD2A18AZ4HWM26211 የሞተር ቁጥር DUZWHM07143 የሊብሬ ቁጥር 000446327 ከላይ የተጠቀሰው የሞተር ሳይክል ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ21/05/2016 ዓ.ም. አመልክተዋል፡ ፡ በመሆኑም ይህን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የባሌ ዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## አማራ ክልል

ንብረትነቱ የቱጃሬ ጨጨላ አያቶ የሆነ አውቶቡስ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ኮድ 03-33703 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በቀን 28/06/2016 ዓ.ም. በተፃፈ አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ይህን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአ/ብ/ክ/መ ደ/ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት**

ጣ/ገብ አቶ ቢኒያም አባይነህ ባሉበት ከሳሽ መ/ታ አወቀ ጌታሁን ጣ/ገብ ቢንያም አባይነህ ተከሳሽ መ/ት ኪነ ንጋቱ መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን ለቀን 27/06/2016 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ3፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍ/ፍ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች አቶ ከበደ ሮቢ ጎበና እና ተጠሪ አቶ ዳንኤል እንድሪስ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 25/06/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ወይንሸት ብርሃኑ እና ተጠሪ አቶ ተመስገን ወልደአምላክ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 28/06/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 7ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች ወ/ሪት ናዲያ ጅዋድ ነስር እና ተጠሪ ወ/ሮ በለጠች ወልዱ ስብሀቱ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነ ተጠሪ ካሉ ያሉበትን የሚያውቅ ሰው ካለ የካቲት 29 ቀን 2016 ዓ.ም በ4፡30 አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት**
**አራዳ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አቶ ስለሺ ሰብስብ ገብረፃዲቅ እና በተከሳሾች 1ኛ ወ/ሮ አይንሸት ሰብስብ ገብረፃዲቅ 2ኛ አቶ በላይነህ ሰብስብ ገብረፃዲቅ 3ኛ ወ/ሮ ትርንጎ ሰብስብ ገብረፃዲቅ መካከል ስላለው ውርስ ክስ ጉዳይ ተከሳሾች በ29/06/2016 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ለመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 1ኛ ውርስ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች አቶ ዳዊት ግደይ እና ተጠሪ ወ/ሮ ኤልሳ ታዲዮስ አርአያ መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 19/06/2016 ዓ.ም. በ3፡45 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 8ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች እነ የማነ ስብሀቱ መሰለ እና ተጠሪ አቶ ሚካኤል አፈወርቅ ተጠሪ ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሉ ወይም ተጠሪ ያሉበትን የሚያውቅ ሰው ካለ ለየካቲት 29 ቀን 2016 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት በአ/አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት**
**አራዳ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካሽ ስኬት ባንክ አክስዮን ማኅበር/የቀድሞው አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ እና በተከሳሾች/ተጠሪዎች 1ኛ ቀሪ አለም አንዱአለም 2ኛ ጌትነት አምደፅዮን 3ኛ በእውቀቱ አንዱአለም መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃ/ቃ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች /ተጠሪዎች በ15/06/2016 ዓ.ም. በ8፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ አቶ ኃ/ገብርኤል ብርሃኑ ዘመንፈስ እና በተከሳሽ አቶ አሸናፊ በላይነህ ሀይሉ መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 18/06/2016 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም አቃቂ መለዋወጫ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-33375 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት ሻንሲ ቁጥር MMBJNK7706FO29705 ሞዴል K77JSEN52 የሞተር ቁጥር 4M40NA0631 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ4/6/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የን/ስ/ላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**